4 መኖሪያው በሰማይ የሆነ እግዚአብሔር
ይስቅባቸዋል ፤
በከንቱ አሳባቸውም ያፌዝባቸዋል ።
5 ቀጥሎም በቍጣው ይገሥጻቸዋል ፤
በመዓቱም ያሸብራቸዋል ።
6 “በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ
ያነገሥሁት ንጉሥ ይህ ነው!”
ይላቸዋል ።

7 ንጉሡም “እነሆ! እግዚአብሔር
የሰጠውን ትእዛዝ ዐውጃለሁ ፤
እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ ፥
‘አንተ ልጄ ነህ ፤ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ፤
8 ለምነኝ ፥ አሕዛብ ሁሉ እንዲገዙልህ
አደርጋለሁ ፤
ምድርም በሙሉ የአንተ ግዛት
ትሆናለች ።
9 በብረት በትር ትሰብራቸዋለህ ፤
እንደ ሸክላ ዕቃም ቀጥቅጠህ
ታደቃቸዋለህ ።’ ”

10 አሁንም እናንተ ነገሥታት ይህን
ማስጠንቀቂያ ስሙ ፤
እናንተ የዓለም መሪዎች ይህን
ተግሣጽ አስተውሉ ፤
11 አክብሮት በተሞላበት ፍርሃት ፥
እግዚአብሔርን አገልግሉት ፤
በመንቀጥቀጥም እርሱን ፍሩት ።
12 ቍጣው ፈጥኖ ከመገለጡና እናንተም
በድንገት ከመጥፋታችሁ በፊት
ስገዱለት ።
እግዚአብሔርን መጠጊያቸው
የሚያደርጉት ሁሉ
የተባረኩ ናቸው ።

## ምዕራፍ 3
### የስደት ጊዜ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ! ጠላቶቼ እንዴት
ብዙዎች ናቸው!
ብዙዎችም በጠላትነት በእኔ ላይ
ተነሥተዋል ፤
2 “እግዚአብሔር አያድነውም” እያሉም
ስለ እኔ ይናገራሉ ።

3 እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ግን ጋሻዬ
ነህ ፤
ድልን በማጐናጸፍ ክብርን የምትሰጠኝ
አንተ ነህ ።
4 እግዚአብሔር እንዲረዳኝ ፥
ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እርሱ
እጮኻለሁ ፤
እርሱም በተቀደሰ ተራራው ላይ ሆኖ
ይሰማኛል ።

5 እኔ ተኛሁ ፥ እንቀላፋሁም ፤
እግዚአብሔር ሌሊቱን ሙሉ
ስለጠበቀኝ ፥
በደኅና ከእንቅልፌ ተነሣሁ ።
6 በዙሪያዬ የከበቡኝን ፥
በብዙ ሺ የሚቈጠሩትን ጠላቶቼን
አልፈራቸውም ።

7 እግዚአብሔር ሆይ! ተነሥ ፤
አምላኬ ሆይ! አድነኝ ፤
ጠላቶቼን ሁሉ የምትቀጣ ፥
እንዳይጐዱኝም ጥርሳቸውን
(ኀይላቸውን) የምትሰባብር ፥
አንተ ነህ ።
8 የማዳን ኀይል የእግዚአብሔር ነው ፤
እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ሕዝብህን
ባርክ!

## ምዕራፍ 4
### እግዚአብሔርን በመታመን የሚቀርብ ጸሎት

1 የመብቴ ጠባቂ የሆንህ እግዚአብሔር
ሆይ!
የልመና ጩኸቴን ስማ ፤
ከዚህ በፊት በተቸገርሁ ጊዜ
ረድተኸኛል ፤
አሁንም ራራልኝ ፥ ጩኸቴንም ስማ ።

2 እናንተ ሰዎች ፥
እስከ መቼ ክብሬን ታዋርዳላችሁ?
እስከ መቼስ ከንቱ ነገርን
ትወድዳላችሁ?
እስከ መቼስ ሐሰትን ትፈልጋላችሁ?

3 እግዚአብሔር ታማኞች የሆኑ ሰዎችን
ለራሱ እንደመረጠ ዕወቁ ፤
ስለዚህ ወደ እርሱ በምጸልይበት ጊዜ
ይሰማኛል ።

4 ምንም ያህል ብትቈጡ ፥ ኃጢአት
አትሥሩ ፤
በምትተኙበት ስፍራ
በጸጥታ ልባችሁን መርምሩ ።

---

2:7 ፦ ሐ.ሥ. 13:33 ፤ ዕብ. 1:5 ፤ 5:5 ። 2:9 ፦ ራእ. 2:26-27 ፤ 12:5 ፤ 19:15 ። 3:1-8 ፦ 2ሳሙ. 15:13-17:22 ።
4:4 ፦ ኤፌ. 4:26 ።

5 ለእግዚአብሔር ትክክለኛውን መሥዋዕት
አቅርቡ ፤
እምነታችሁንም በእርሱ ላይ
አድርጉ ።

6 "መልካሙን ነገር ማን ያሳየናል?"
የሚሉ ብዙዎች ናቸው ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ!
በርኅራኄ ተመልከተን ።
7 ለእኔ የሰጠኸኝ ደስታ ግን ፥
ሌሎች በብዙ እህልና በብዙ ወይን
ከሚያገኙት ደስታ የበለጠ ነው ።

8 እግዚአብሔር ሆይ!
በሰላም እንድኖር የምታደርገኝ አንተ
ብቻ ስለሆንኽ ፥
በምተኛበት ጊዜ በሰላም
እንቀላፋለሁ ።

## ምዕራፍ 5

### የመማጸኛ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ! ቃሌን አድምጥ ፤
መቃተቴንም (የሚያሰጨንቀኝንም
ውስጣዊ አሳብ) ተመልከት ።
2 ንጉሤና አምላኬ ሆይ!
የምጸልየው ወደ አንተ ስለሆነ ፥
ጸሎቴን አድምጥ ።

3 እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ ፤
እኔም በማለዳ ልመናዬን ወደ አንተ
አቅርቤ
መልሱን እጠባበቃለሁ ።

4 አንተ በኃጢአት የምትደሰት አምላክ
አይደለህም ፤
ክፉዎችም ከአንተ ጋር አይኖሩም ፤
5 ትዕቢተኞች በፊትህ አይቆሙም ፤
ዐመፀኞችንም ሁሉ ትጠላለህ ፤
6 ሐሰት የሚናገሩትን ሁሉ ታጠፋለህ ፤
ሰው የሚገድሉትንና አታላዮችን
ትጸየፋለህ ።

7 እኔ ግን ከዘላለማዊ ፍቅርህ ብዛት
የተነሣ ፥
ወደ ቤትህ እገባለሁ ፤
በተቀደሰው መቅደስህ እጸልያለሁ ፤
አክብሮት በተሞላበት ፍርሃትም
እሰግድልሃለሁ ።

8 እግዚአብሔር ሆይ!
የሚጠባበቁኝ ጠላቶቼ ብዙዎች
ናቸው ፤
ስለዚህ ፈቃድህን እንዳደርግ ምራኝ ፤
መንገድህንም በፊቴ አቅናልኝ ።

9 ጠላቶቼ የሚናገሩት ሁሉ ከእውነት
የራቀ ስለሆነ ፥
ከአፋቸው እውነት አይገኝም ፤
አሳባቸውም በተንኰል የተሞላ ነው ፤
ጉሮሮአቸውም እንደተከፈተ መቃብር
ነው ፤
በምላሳቸውም ሰውን ያታልላሉ ።
10 አምላክ ሆይ! ፍረድባቸው ፥
ቅጣቸውም ፤
የራሳቸው ሤራ መጥፊያቸው ይሁን ፤
ኃጢአታቸው ስለበዛና በአንተም ላይ
ስላመፁ ፥
ከፊትህ አስወግዳቸው ።

11 በአንተ የሚተማመኑ ሁሉ ግን ደስ
ይላቸዋል ፤
ዘወትር በደስታ "እልል" ይላሉ ፤
በአንተ ተመክተው በእውነት
እንዲደሰቱ ፥
የሚወዱህን ሁሉ ጠብቃቸው ።
12 እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ የሚታዘዙህን ጻድቃን
ትባርካለህ ፤
ቸርነትህም እንደ ጋሻ መከላከያ
ይሆንላቸዋል ።

## ምዕራፍ 6

### የችግር ጊዜ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ! በቍጣህ
አትቅሠፈኝ ፤
በመዓትህም አትገሥጸኝ ።
2 እግዚአብሔር ሆይ!
ጕልበቴ አልቆአልና ራራልኝ ፤
አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ ፤
ፈጽሞ ደክሜአለሁና ብርታትን
ስጠኝ ።

3 እግዚአብሔር ሆይ!
ሰውነቱ በሙሉ እጅግ ታውኮአል ፤
ታዲያ እኔን ከመርዳት የምትዘገየው
እስከ መቼ ነው?
4 እግዚአብሔር ሆይ!
ወደ እኔ ተመለስ ፤ እርዳኝም ፤
በምሕረትህም አድነኝ ።

5፥9 ፦ ሮም 3፥13 ። 6፥1 ፦ መዝ. 38፥1 ።

የድኾችም ተስፋ ከንቱ ሆኖ ለዘላለም
አይቀርም ።

19 አምላክ ሆይ! ሰዎች በብርታታቸው
እንዳይኰሩብህ ተነሥ!
አሕዛብን በፊትህ ሰብስብ ፤
በእነርሱም ላይ ፍረድ ።
20 እግዚአብሔር ሆይ!
እንዲፈሩህና ከሞት የማያመልጡ
ሰብአዊ ፍጡሮች መሆናቸውንም
እንዲያውቁ አድርጋቸው ።

## ምዕራፍ 10

ትክክለኛ ፍርድ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ!
ስለምን እንደዚህ ራቅህ?
በችግር ጊዜስ ስለምን ትሰወራለህ?
2 ክፉ ሰዎች ይታበያሉ ፤ ድኾችንም
ያሳድዳሉ ፤
ለሌሎች ባጠመዱት ወጥመድ
ራሳቸው ይግቡበት ።

3 ኃጢአተኛ በክፉ ምኞቱ ይመካል ፤
ስግብግብ ሰውም ይራገማል ፤
እግዚአብሔርንም ይክዳል ።
4 ኃጢአተኛ ስለ እግዚአብሔር ግድ
የለውም ፤
በትዕቢቱም "እግዚአብሔር የለም"
ብሎ ያስባል ።

5 ይህም ሆኖ ፤ ሁሉ ነገር ይሳካለታል ፤
ትዕቢተኛም ስለሆነና የእግዚአብሔር
ሕግ
ከእርሱ አስተሳሰብ የራቀ ስለሆነ
ሊያስተውለው አይችልም ፤
በጠላቶቹም ላይ ያፌዛል ።
6 "እኔ ከቶ አልዋረድም ፤
ችግርም ሳይደርስብኝ እኖራለሁ"
ብሎ ያስባል ።
7 ንግግሩም በእርግማን ፤ በሐሰትና በዛቻ
የተሞላ ነው ፤
በተንኰልና በክፋት የተሞሉ ቃላትን
ለመናገር ይቸኩላል ።

8 ንጹሓችን ሰዎች በስውር ለመግደል
በየመንደሩ ያደፍጣል ፤
ምስኪኖችንም ለማጥመድ
አትኩሮ ያያል ።
9 በሚያደፍጥበትም ስፍራ
እንደ አንበሳ አድብቶ ይጠባበቃል ፤
ድኾችንም ለመያዝ ይሸምቃል ፤
በወጥመዱም ይይዛቸዋል ፤
እየጐተተም ይወስዳቸዋል ።

10 በሚመታቸው ጊዜ ጎይሉ
ስለሚበረታባቸው ፤
ምስኪኖች ተሸንፈው ይወድቃሉ ።
11 ኃጢአተኛ በአሳቡ ፤
"እግዚአብሔር እኔን ምንም
አያደርገኝም ፤
ዐይኖቹን ጨፍኖአል ፤ ከቶም
አያየኝም" ይላል ።

12 እግዚአብሔር ሆይ! ተነሥ
እነዚያን ክፉ ሰዎች ቅጣቸው ፤
የተጨቈኑትን አስታውሳቸው ።
13 ኃጢአተኛ ሰው እግዚአብሔርን ስለምን
ይንቃል?
በአሳቡስ "እግዚአብሔር
አይቀጣኝም" ለምን ይላል?

14 አንተ ግን በእርግጥ ታያለህ ፤
ችግርንና ሥቃይን ትመለከታለህ ፤
ሁልጊዜም ለመርዳት ዝግጁ ነህ ፤
አንተ አባትና እናት የሌላቸውን ልጆች
ዘወትር ስለምትረዳ ፤
ምስኪኖች ሁሉ እንድትረዳቸው
ወደ አንተ ይቀርባሉ ።
15 የኃጢአተኞችንና የክፉ ሰዎችን ኀይል
አድክም ፤
ከእንግዲህ ወዲያ ክፋትን እንዳያደርጉ
በክፉ ሥራቸው ሁሉ ቅጣቸው ።

16 እግዚአብሔር ለዘላለም ንጉሥ ሆኖ
ይኖራል ፤
ለሌሎች አማልክት የሚሰግዱ ሕዝቦች
ግን
ከምድሩ ይጠፋሉ ።
17 እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ የምስኪኖችን ጸሎት ትሰማለህ ፤
ልመናቸውንም አድምጠህ
ታበረታታቸዋለህ ፤
18 የጭቁኖችንና አባትና እናት የሌላቸውን
ልጆች
ጩኸት ትሰማለህ ፤
ስእነርሱም ትፈርድላቸዋለህ ፤
ስለዚህ ከዐፈር የተፈጠሩ ከንቱ የሆኑ
ሰዎች
ከእንግዲህ ወዲህ
አያስጨንቁአቸውም ።

10፡7 ፡- ሮም 3፡14 ።

ከሙቀቱም ኀይል ሊያመልጥ የሚችል
ምንም ነገር የለም ።

### የእግዚአብሔር ሕግ

7 የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው ፤
ለነፍስ አዲስ ሕይወትን ይሰጣል ፤
የእግዚአብሔር ትእዛዝ የታመነ ነው ፤
ማስተዋል ለጐደላቸው ጥበብን
ይሰጣል ።
8 የእግዚአብሔር ሥርዓት ትክክል ነው ፤
ለልብ ደስታን ይሰጣል ፤
የእግዚአብሔር ትእዛዝ ንጹሕ ነው ፤
ለአእምሮ የዕውቀትን ብርሃን
ይሰጣል ።
9 እግዚአብሔርን በፍርሃት ማገልገል
መልካም ነገር ነው ፤
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል ፤
የእግዚአብሔር ሥርዓት ምንም እንከን
የሌለበት
እውነትና ትክክል ነው ።
10 ከወርቅ ፤ እንዲያውም ከተጣራ ንጹሕ
ወርቅ ይልቅ የተወደደ ነው ፤
ከማር ፤ እንዲያውም ከማር ወለላ
ይልቅ
የጣፈጠ ነው ።
11 ለእኔም ለአገልጋይህ ማስጠንቀቂያ
ይሆነኛል ፤
ሕግህንም በመጠበቅ ብዙ ጥቅም
አገኛለሁ ።

12 የራሱን ስሕተት የሚያይ ማንም የለም ፤
አምላኬ ሆይ! ከተሰወረ በደል
አንጻኝ ።
13 ኃጢአት በእኔ ላይ እንዲሠለጥን
አታድርግ ፤
በድፍረት ኃጢአት ከመሥራትም
ጠብቀኝ ፤
በዚያን ጊዜ ከታላቅ ኃጢአት ርቄ
ፍጹም ለመሆን እችላለሁ ።

14 እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ መጠጊያዬና ቤዛዬ ነህ ፤
ንግግሬም ሆነ አሳቤ ፤
በአንተ ዘንድ የተወደደ ይሁን ።

## ምዕራፍ 20

### ድል ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

1 በተቸገርህ ጊዜ ፤
እግዚአብሔር ልመናህን ይስማህ ፤
የያዕቆብ አምላክ ይጠብቅህ!
2 ከመቅደሱ በረከትን ይላክልህ ፤
በጽዮን ተራራም ሆኖ ይርዳህ ።
3 መባህን ሁሉ ይቀበልልህ ፤
በመሥዋዕትህም ደስ ይበለው ።
4 የልብህን ምኞት ይስጥህ ፤
አሳብህን ሁሉ ይፈጽምልህ ፤
5 በዚያን ጊዜ አንተ ስላገኘኸው ድል ፤
በደስታ "እልል!" እንላለን ፤
የበዓል ቀን እያደረግንም ፤
እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ፤
እግዚአብሔር የለመንኸውን ሁሉ
ይስጥህ ።

6 እግዚአብሔር መርጦ ለቀባው ንጉሥ ፤
ድል እንደሚሰጠው አሁን ዐወቅሁ ፤
በቅዱስ መኖሪያው በሰማይ ሆኖ
ይሰማዋል ፤
በኀይሉም ታላላቅ ድሎችን
ይሰጠዋል ።
7 አንዳንዶች በጦር ሠረገላዎቻቸው ፤
ሌሎችም በፈረሶቻቸው ይመካሉ ፤
እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር
ኀይል
እንታመናለን ።
8 እነርሱ ተሰናክለው ይወድቃሉ ፤
እኛ ግን እንነሣለን ፤ ጸንተንም
እንቆማለን ።

9 አምላክ ሆይ!
ንጉሡን ከጠላቶቹ እጅ አድነው ፤
እኛም በምንጠራህ ጊዜ ስማን ።

## ምዕራፍ 21

### ድል ስለማግኘት የቀረበ ምስጋና

1 አምላክ ሆይ!
ኀይልን ስለሰጠኸው ፤ ንጉሥ ደስ
ብሎታል ፤
ድልን ስለ አቀዳጀኸውም ሐሴት
ያደርጋል ።
2 የልቡን ምኞት ሰጥተኸዋል ፤
የለመነህንም ፈጽመህለታል ።

3 ብዙ በረከት ይዘህ ደረስህለት ፤
በራሱ ላይ የንጹሕ ወርቅ ዘውድ
ደፋህለት ።
4 ሕይወትን እንድትሰጠው ለመነህ ፤
አንተም ረዥም ዕድሜና
ዘላለማዊ የሆነ ሕይወትን ሰጠኸው ።
5 አንተ ስለረዳኸውም ታላቅ ክብር አገኘ ፤
ስመ ጥሩነትንና ግርማን አቀዳጀኸው ።
6 የአንተ በረከት ዘላለም ከእርሱ ጋር ነው ፤
አንተም ከእርሱ ጋር በደስታ
ስለመገኘትህ
ደስ ታሰኘዋለህ ፤

21 ከእነዚህ እንደ አንበሶች ከሆኑ ሰዎች አፍ
አድነኝ ፤
እንደ ተዋጊ በሬ ጨካኝ ከሆኑ ሰዎች
ጠብቀኝ ።

22 የስምህን ታላቅነት ለወገኖቼ እነግራለሁ ፤
እነርሱ በተሰበሰቡበት ስፍራ
አመሰግንሃለሁ ፤
እንዲህም እላለሁ ፦
23 "እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈሩት
አመስግኑት ፤
እናንተ የያዕቆብ ዘሮች አክብሩት ፤
እናንተ የእስራኤል ዝርያዎች
አገልግሉት ።
24 እርሱ ድኾችን አይንቅም ፤
ሥቃያቸውንም ቸል አይልም ፤
ከእነርሱ አይርቅም ፤
ወደ እርሱ በሚጮኹበትም ጊዜ
ይሰማቸዋል ።"

25 ስለ ሠራኸው መልካም ሥራ ፤
ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ
አመሰግንሃለሁ ፤
በሚያገለግሉህ ሰዎች ፊት ሆኜ ፦
የተሳልሁልህን መሥዋዕት
አቀርብልሃለሁ ።
26 ድኾች እስኪጠግቡ ይበላሉ ፤
ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡም
ያመሰግኑታል ፤
እነርሱም ለዘላለም ይበለጽጋሉ ።

27 መንግሥታት ሁሉ እግዚአብሔርን
ያስታውሱታል ፤
በዓለም ዙሪያ ያሉት ሁሉ ወደ እርሱ
ይመለሳሉ ፤
የአረማውያን ነገዶች ሁሉ በፊቱ
ይሰግዳሉ ።
28 መንግሥታዊ ሥልጣን ሁሉ
የእግዚአብሔር ነው ፤
ስለዚህ መንግሥታትን ሁሉ
የሚያስተዳድር እርሱ ነው ።

29 በዓለም የሚኖሩ ባለጸጎች ሁሉ በዓል
በማድረግ
ለእርሱ ይሰግዳሉ ፤
ከሞት የማያመልጡ ሰብአዊ ፍጡሮች
ሁሉ
በፊቱ ይንበረከካሉ ።
30 መጪው ትውልድ ያገለግለዋል ፤
ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራ
ለተተኪው ትውልድ ይናገራሉ ።

31 ገና ላልተወለዱትም ፦
"እግዚአብሔር ሕዝቡን አዳነ"
ተብሎ ይነገራቸዋል ።

## ምዕራፍ 23
### እግዚአብሔር እረኛዬ ነው

1 እግዚአብሔር እረኛዬ ስለሆነ ፦
የሚያስፈልገኝን ሁሉ አላጣም ።
2 በለመለመ መስክ እንዳርፍ ያደርገኛል ፤
ጸጥ ወዳለ ጥሩ ውሃ ይመራኛል ።
3 ሕይወቴን ያድሳል ፤
ስለ ስሙም በትክክለኛ መንገድ
ይመራኛል ።
4 አምላክ ሆይ! አንተ ከእኔ ጋር ስለሆንህ ፦
ለሞት በሚያስፈራ ጥቅጥቅ ጨለማ
ባለበት
ሸለቆ ውስጥ ባልፍ እንኳ ፦
ክፉ ነገር ይደርስብኛል ብዬ አልፈራም ፤
የጠባቂነትህ በትርና ምርኩዝ
ያጽናኑኛል ።

5 ጠላቶቼ እኔን በሚመለከቱበት ፦
ታላቅ ግብዣ አዘጋጀህልኝ ፤
እንደ ክብር እንግዳ
ራሴን በዘይት ቀብተህ ተቀበልኸኝ ፤
እስኪትረፈረፍ ድረስ ፦ ጽዋዬን
ሞላህልኝ ።
6 ደግነትህና ፍቅርህ በሕይወቴ ዘመን
ሁሉ ፦
እንደማይለዩኝ እርግጠኛ ነኝ ፤
አምላኪ ሆይ!
ለዘላለምም በቤትህ እኖራለሁ ።

## ምዕራፍ 24
### ታላቁ ንጉሥ

1 ምድርና በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉ ፦
የእግዚአብሔር ናቸው ፤
ዓለምና በውስጥዋ ያሉት ሁሉ
የእርሱ ናቸው ።
2 ምድርን በባሕር ላይ ያቆመ ፦
መሠረትዋንም ጥልቀት ባላቸው
ውቅያኖሶች ውስጥ ያደረገ ፤
ራሱ እግዚአብሔር ነው ።

3 ወደ እግዚአብሔር ተራራ
ሊወጣ የሚችል ማን ነው?
በተቀደሰ መቅደሱስ ሊቆም የሚችል
ማን ነው?
4 ይህን ማድረግ የሚችል ፦

---

22፡22 ፦ ዕብ. 2፡12 ። 23፡2 ፦ ራእ. 7፡17 ። 24፡1 ፦ 1ቆሮ. 10፡26 ። 24፡4 ፦ ማቴ. 5፡8 ።

ጠላቶቼ ብዙዎች ስለሆኑም ፥
ሰላማዊ በሆነ መንገድ ምራኝ ።
12 በውሸትና በዛቻ ለሚያጠቁኝ ጠላቶቼ
አሳልፈህ አትስጠኝ ።

13 ሕያዋን በሚኖሩባት ምድር እስካለሁ
ድረስ ፥
የእግዚአብሔርን ቸርነት እንደማይ
እተማመናለሁ ።
14 በእግዚአብሔር ታመን ፤
በርታ ፥ ተስፋ አትቊረጥ ፤
በእግዚአብሔር ታመን ።

## ምዕራፍ 28

*ዕርዳታ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት*

1 መከታዬ የሆንህ እግዚአብሔር ሆይ!
ወደ አንተ ስጣራ ጩኸቴን ስማ ፤
አንተ ካልሰማኸኝ ግን ወደ መቃብር
ከሚወርዱት
እንደ አንዱ መሆኔ ነው ።
2 ዕርዳታህን ፈልጌ ወደ አንተ ስጮኽ
ስማኝ ፤
እጆቼን ወደ ተቀደሰው መቅደስህ
ዘርግቼ ስጸልይ አድምጠኝ ።
3 በልባቸው ጥላቻ እያለ በአፋቸው ወዳጅ
ከሚመስሉና
ዐመፅ ከሚያደርጉ ክፉ ሰዎች ጋር
አታጥፋኝ ።

4 ስለፈጸሙት በደል ተበቀላቸው ፤
በእጃቸው ስለፈጸሙት ክፉ ሥራ
ፍረድባቸው ፤
ተገቢ ቅጣታቸውንም ስጣቸው ።
5 እነርሱ የእግዚአብሔርን ሥራ ችላ
ስላሉና
ያደረገውን ሁሉ ስለረሱ ፥
ይደመስሳቸዋል ፤
እንደገናም አይመሠርታቸውም ።

6 የልመናዬን ጩኸት ስለሰማኝ ፥
እግዚአብሔር ይመስገን ።
7 እግዚአብሔር ኀይሌና ጋሻዬ ነው ፤
ስለሚረዳኝና ደስ ስለሚያሰኘኝም
በእርሱ እተማመናለሁ ፤
ደስ በሚያሰኙ መዝሙሮችም
አመሰግነዋለሁ ።

8 እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል ፤
መርጦ የቀባውንም ንጉሥ
ይደግፈዋል ፤ ያድነዋልም ።

9 አምላክ ሆይ! ሕዝብህን አድን ፤
የአንተ የሆኑትንም ባርክ ፤
እረኛቸውም ሁን ፤
ለዘላለምም ተንከባከባቸው ።

## ምዕራፍ 29

*የእግዚአብሔር ድምፅ በማዕበል ውስጥ ይሰማል*

1 እናንተ በሰማይ ያላችሁ ፍጥረቶች ፥
እግዚአብሔርን አመስግኑት ፤
ስለ ክብሩና ስለ ኀይሉም
አመስግኑት ።
2 ክብር የሚገባውን የእግዚአብሔርን ስም
አመስግኑ ፤
የቅድስናው ክብር በሚገለጥበት ጊዜም
ለእግዚአብሔር ስገዱ ።

3 የእግዚአብሔር ድምፅ በባሕሮች ላይ
ይሰማል ፤
ክቡር የሆነ እግዚአብሔር
እንደ ነጐድጓድ ሲያስገመግም ፤
ድምፁ በውቅያኖስ ላይ ያስተጋባል ።
4 የእግዚአብሔር ድምፅ ፥
በታላቅ ኀይልና በታላቅ ግርማ
ይሰማል ።

5 የእግዚአብሔር ድምፅ ፥ ዝግባዎችን
ይሰብራል ፤
የሊባኖስንም ዝግባዎች ሳይቀር
ይሰብራል ።
6 የሊባኖስን ተራራዎች እንደ እንቦሳ
እንዲፈነጩ ያደርጋቸዋል ፤
የስርዮንንም ተራራ
እንደ ኮርማ እንዲዘል ያደርገዋል ።

7 የእግዚአብሔር ድምፅ ፥
የመብረቅ እሳት እንዲንበለበል
ያደርጋል ።
8 የእግዚአብሔር ድምፅ ፥ በረሓን
ያናውጣል ፤
የቃዴስንም በረሓ ያንቀጠቅጣል ፤
9 የእግዚአብሔር ድምፅ ፥ ወርካዎችን
ያንቃንቃል ፤
የዛፎችን ቅጠል ያረግፋል ፤
በመቅደሱም ያሉ ድምፁን ሲሰሙ ፥
"ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን"
ይላሉ ።

10 እግዚአብሔር በጥልቅ ውሃዎች ላይ
ሥልጣን አለው ፤
እርሱ ለዘላለም ንጉሥ ነው ።

28፥4 ፦ ራእ. 22፥12 ። 29፥1-2 ፦ መዝ. 96፥7-9 ።

11 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኀይልን ይሰጣል ፤
በሰላም ይባርካቸዋል ።

## ምዕራፍ 30
### የምስጋና ጸሎት

1 አምላክ ሆይ!
ስላዳንኸኝና ጠላቶቼ በእኔ ላይ
እንዲደሰቱ
ስላላደረግህ ፥ አመሰግንሃለሁ ።
2 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ!
እንድትረዳኝ ወደ አንተ ተጣራሁ ፤
አንተም ፈወስኸኝ ።
3 ወደ ሲኦል ከመውረድ አዳንኸኝ ፤
ወደ መቃብር ከመውረድ ጠበቅኸኝ ።

4 ታማኞች አገልጋዮቹ የሆናችሁ ሁሉ ፤
እግዚአብሔርን በዝማሬ አመስግኑ ፤
ቅድስናውንም በማሰብ ፤
ምስጋና አቅርቡለት ።
5 እርሱ የሚቈጣው ለጥቂት ጊዜ ነው ፤
ቸርነቱ ግን ለዘላለም ነው ፤
ሌሊት ሲለቀስ አድሮ ፥
በማለዳ ደስታ ይሆናል ።

6 ዋስትና እንዳለኝ ስላወቅሁ ፥
“ከቶ አልሸነፍም” አልሁ ።
7 እግዚአብሔር ሆይ!
በተራራ ላይ እንዳለ ምሽግ ፥
አጽንተህ አቆምኸኝ ፤
ከእኔ በተሰወርህ ጊዜ ግን ደነገጥሁ ።

8 እግዚአብሔር ሆይ! አንተን ጠራሁ ፤
እንድትረዳኝም ተማጸንኩህ ።
9 እኔ ብሞት ምን ትጠቀማለህ?
ወደ መቃብር ብወርድስ ምን ትርፍ
ታገኛለህ?
የሞቱ ሰዎች ሊያመሰግኑህ ይችላሉን?
ስለማያቋርጠው ቸርነትህስ መመስከር
ይችላሉን?
10 እግዚአብሔር ሆይ! ስማኝ ፥ ማረኝም ፤
እግዚአብሔር ሆይ! እርዳኝ!

11 አንተ ሐዘኔን ወደ ደስታ ለወጥኽልኝ ፤
ትካዜዬን ከእኔ አስወገድህልኝ ፤
በደስታም ሞላኸኝ ።
12 ስለዚህ ዝም አልልም ፤
ለአንተ የምስጋና መዝሙር
አቀርባለሁ ፤
እግዚአብሔር ሆይ! አንተ አምላኬ ነህ ፥
ስለዚህ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ ።

## ምዕራፍ 31
### በእግዚአብሔር የመታመን ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ!
መጠጊያ እንድትሆነኝ ወደ አንተ
መጥቻለሁ ፤
ስለዚህ በጠላቶቼ በመሸነፍ እንዳፍር
አታድርገኝ ፤
በጽድቅህም አድነኝ ።
2 ፈጥነህ ስማኝ ፥ ታደገኝም ፤
አንተ የእኔ ጠባቂና አዳኝ ስለሆንህ ፥
መጠጊያ ምሽግ ሁነኝ ።

3 አንተ መጠጊያ ምሽጌ ነህ ፤
ስለ ስምህ ስትል ምራኝ ፤
የምሄድበትንም መንገድ አሳየኝ ።
4 አንተ መጠጊያዬ ስለሆንህ ፥
ጠላቶቼ ከዘረጉብኝ ወጥመድ
አውጣኝ ።
5 የእውነት አምላክ የሆንህ እግዚአብሔር
ሆይ!
ሕይወቴን ለአንተ ዐደራ ስለሰጠሁ
አድነኝ ።

6 አንተ ለሐሰተኞች አማልክት ፥
የሚሰግዱትን ሁሉ ትጠላለህ ፤
እኔ ግን በአንተ እታመናለሁ ።
7 ስለማያቋርጠው ፍቅርህ ደስ ይለኛል ፤
በደስታም እፈነድቃለሁ ፤
አንተ መከራዬን ተመልክተሃል ፤
ችግሬንም ዐውቀሃል ።
8 ለጠላቶቼ አሳልፈህ አልሰጠኸኝም ፤
ይልቁንም ወደፈለግሁበት ስፍራ
እንድሄድ ፥
ሰፊ መንገድ ከፈትህልኝ ።

9 እግዚአብሔር ሆይ! በችግር ላይ
ስለሆንሁ ፥
ምሕረትን አድርግልኝ ፤
በለቅሶ ብዛት ዐይኖቼ ደከሙ ፤
እጅግ ተጐሳቍዬአለሁ ።
10 ከሐዘን ብዛት የተነሣ ፤ ወደ ሞት
ተቃረብሁ ፤
ለቅሶም ዕድሜዬን አሳጠረ ፤
ከመከራዬ ብዛት የተነሣ ደከምሁ ፤
አጥንቶቼም ደቀቁ ።

11 ጠላቶቼ ሁሉ ፥ ይልቁንም ጐረቤቶቼ
በንቀት ይመለከቱኛል ፤
የሚያውቁኝም ሁሉ ይጸየፉኛል ፤
በመንገድ ሲያዩኝም ከእኔ ይሸሻሉ ።

31፥5 ፦ ሉቃ. 23፥46 ።

6-7 እዚህ በስደት ላይ ሳለሁ
ልቤ በሐዘን ተሰብሮአል ፤
ስለዚህ አሳቤን ወደ እርሱ
እመልሳለሁ ።
እርሱ የሐዘን ማዕበል ወደ እኔ ልኮአል ፤
ሁከት እንደ ጐርፍ እያስገመገመ
ወደ እኔ ደርሶአል ፤
ከሔርሞንና ከሚዛር ተራራዎች
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እንደሚወርድ
ፏፏቴ ይጮኻል ።
8 እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅሩን
ዕለት በዕለት ያሳያል ፤
ስለዚህ እኔ ወደ ሕይወቴ አምላክ
እጸልያለሁ ፤
በሌሊትም የምስጋና መዝሙር
አቀርብለታለሁ ።

9 መጠጊያዬ የሆነውን አምላክ
"ስለምን ረሳኸኝ?
ጠላቶቼ ከሚያደርሱብኝ ጥቃት
የተነሣ
ስለምን ስተክዝ እኖራለሁ?"
እለዋለሁ ።
10 እነርሱ "አምላክህ የት አለ?" እያሉ
ይዘባበቱብኛል ፤
ሰውነቴ በስጋት እስኪደቅ ድረስ
ዘወትር ይሰድቡኛል ።

11 ለምን እንዲህ አዝናለሁ?
ለምንስ እንደዚህ እጨነቃለሁ?
ተስፋዬን በእግዚአብሔር አደርጋለሁ ፤
አዳኜንና አምላኬን እንደገና
አመሰግናለሁ ።

## ምዕራፍ 43
የስደት ጊዜ ጸሎት
(ከመዝሙር 42 የሚቀጥል)

1 አምላክ ሆይ! ፍረድልኝ ፤
ከእውነት በራቁ አረማውያን ፊት
ስለ እኔ ተከራከርልኝ ፤
ከሐሰተኞችና ከክፉ ሰዎች እጅ አድነኝ ።
2 መጠጊያዬ አንተ ነህ ፤
ታዲያ ስለምን ትተወኛለህ?
ጠላቶቼ ከሚያደርሱብኝ ጥቃት የተነሣ
ስለምን ስተክዝ እኖራለሁ?

3 ብርሃንህንና እውነትህን ላክ ፤
እነርሱ እየመሩ ወደ ተቀደሰው
ተራራህ ወደ ጽዮን ፥
መኖሪያህ ወደሆነው መቅደስህም
መልሰው ያምጡኝ ።
4 አምላክ ሆይ!
በዚያን ጊዜ ወደ መሠዊያህ
እሄዳለሁ ፤
መጠን የሌለው ደስታ የማገኘው
ከአንተ ነው ፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ!
በገናዬን እየደረደርሁ
የምስጋና መዝሙር ለአንተ
አቀርባለሁ ።
5 ለምን እንዲህ አዝናለሁ?
ለምንስ እንደዚህ እጨነቃለሁ?
ተስፋዬን በእግዚአብሔር አደርጋለሁ ፤
አዳኜንና አምላኬን እንደገና
አመሰግናለሁ ።

## ምዕራፍ 44
የመማጸኛ ጸሎት

1 አምላክ ሆይ!
በጥንት ዘመን ያደረግኸውን ሁሉ
በጆሮአችን ሰማን ፤
የቀድሞ አባቶቻችንም በዘመናቸው
ስላደረግህላቸው ድንቅ ነገሮች ሁሉ
ነግረውናል ።
2 አንተ ራስህ አረማውያንን
ከርስታቸው ነቅለህ አባረርህ ፤
ሕዝብህን በእነርሱ ምድር ላይ
ተከልህ ፤
ሌሎችን መንግሥታት ቀጣህ ፤
የራስህን ሕዝብ ግን አበለጸግህ ።
3 እነርሱ ምድርን የወረሱት ፥ በሰይፋቸው
አይደለም ፤
ድል አድርገው የወሰዱትም ፥
በራሳቸው ኀይል አይደለም ፤
ይህን ሁሉ ያደረጉት አንተ
ስለወደድሃቸውና
ከእነርሱም ጋር በመሆን በኀይልህና
በብርታትህ
ስለረዳሃቸው ነው ።

4 አንተ ንጉሤና አምላኬ ነህ ፤
የያዕቆብ ዘር ለሆነው ሕዝብህ ፥
ድልን የምታጐናጽፍ አንተ ነህ ።
5 በአንተ ዕርዳታ ጠላቶቻችንን ድል
እንነሣለን ፤
በስምህም ተቃዋሚዎቻችንን
እንረግጣለን ።
6 ቀስቴም ሆነ ሰይፌ ያድነኛል ብዬ
አልተማመንበትም ።
7 ከጠላቶቻችን የምታድነን አንተ ነህ ፤
የሚጠሉንንም የምታዋርድልን አንተ
ነህ ።
8 ስለዚህ ዘወትር በአንተ እንመካለን ፤
ስምህንም ለዘላለም እናመሰግናለን ።

9 አሁን ግን ጣልኸን፥ አሳፈርኸንም፤
ከሚዘምተው ሠራዊታችን ጋር
አብረህ መውጣትን ትተሃል።
10 ከጠላቶቻችን ፊት እንድንሸሽ
አደረግኸን፤
ጠላቶቻችንም ያለንን ሀብት ሁሉ
ዘረፉን።
11 እንደ በጎች እንድንታረድ አደረግኸን፤
በአረማውያን ምድር በተንኸን።
12 ሕዝብህን እንደ ርካሽ ነገር ቈጠርኸው፤
በአነስተኛ ዋጋም ሸጥኸው።
13 ለጎረቤቶቻችን መሳለቂያ አደረግኸን፤
በዙሪያችን ላሉትም መዘባበቻና
መሳቂያ አደረግኸን።
14 በአረማውያን መካከል መተረቻ
አደረግኸን፤
እነርሱም በንቀት ራሳቸውን
ይነቀንቁብናል።
15 እኔ ዘወትር እንደተዋረድሁ እኖራለሁ፤
በሐፍረትም ተሸፍኛለሁ፤
16 እንዲህም የሆንሁት፤
የጠላቶቼንና የሚበቀሉኝን ሰዎች
ዛቻና ስድብ ስለምሰማ ነው።

17 ይህም ሁሉ የደረሰብን
አንተን ሳንረሳና ቃል ኪዳንህንም
ሳናፈርስ ነው።
18 ለአንተ ያለንን ታማኝነት አላጓደልንም፤
ትእዛዝህንም አልተላለፍንም።
19 ነገር ግን በአራዊት መካከል ጣልኸን፤
ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ውስጥም
ተውኸን።

20 አምላካችንን ማምለክ ትተን
ወደ ባዕዳን አማልክት ለመጸለይ
እጆቻችንን ዘርግተን ቢሆን፥
21 አንተ የተሰወረውን አሳባችንን
ስለምታውቅ
በደላችንን ገልጠህ ባየህብን ነበር።
22 ነገር ግን በየቀኑ የምንገደለውና
እንደሚታረዱ በጎች የምንቈጠረው፥
ስለ አንተ ፍቅር ነው።

23 ጌታ ሆይ! ንቃ! ስለምንስ ታንቀላፋለህ?
ለዘላለምም አትጣለን።
24 ሥቃያችንንና ችግራችንን ቸል በማለት
ስለምን ከእኛ ትሰወራለህ?

25 ተሰባብረን መሬት ላይ ወድቀናል፤
ተሸንፈንም ትቢያ ላይ ተዘርረናል።
26 አምላክ ሆይ!
ተነሥ፥ እርዳን! ስለ ዘላለማዊው
ፍቅርህም
ነፃነትን ስጠን።

## ምዕራፍ 45

### የፍቅር ቅኔ

1 ከልቤ መልካም ቃላት በማፍለቅ
ስለ ንጉሡ ክብር እቀኛለሁ፤
የጥሩ ጸሐፊ ብዕር ለመጻፍ
እንደሚፈጥን፤
የእኔም አንደበት ቅኔ ለመቀኘት
ይፈጥናል።

2 አንተ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ
የተዋብህ ነህ፤
ንግግርህም ሞገስ የሞላበት ነው፤
የእግዚአብሔር በረከት ተለይቶህ
አያውቅም።
3 በክብርና በግርማ የተሞላህ
ኀያል ንጉሥ ሆይ!
ሰይፍህን ታጥቀህ ተዘጋጅ።

4 እውነትና ምሕረት የሞላበት ፍትሕ
እንዲከበር፥
ግርማን ተጐናጽፈህ ድል ለማድረግ
ገሥግሥ፤
ኀይልህም ታላላቅ ድሎችን ያስገኛል።
5 ፍላጻዎችህ የተሳሉ ናቸው፤
የጠላቶችህንም ልብ ይወጋሉ፤
መንግሥታትም ተሸንፈው በእግርህ ሥር
ይወድቃሉ።

6 አምላክ ሆይ!
መንግሥትህ ዘላለማዊ ነው፤
የመንግሥትህም በትር የቅንነት በትር
ነው።
7 አንተ መልካሙን ነገር ትወድዳለህ፤
ክፉውን ነገር ትጠላለህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ መረጠህ፤
ከሌሎች ነገሥታትም ይበልጥ
የደስታን ዘይት ቀባህ።
8 ከከርቤና ከዝባድ የተሠራ ሽቶ
በልብስህ ላይ ተርከፍክፎአል፤
መዘምራን በዝሆን ጥርስ ባጌጠው
ቤተ መንግሥትህ ተገኝተው
ያስደስቱሃል።
9 በቤተ መንግሥትህ ከሚገኙት ወይዛዝርት
መካከል፥
የነገሥታት ሴቶች ልጆች ይገኛሉ፤
ንግሥቲቱም በንጹሕ ወርቅ ያሸበረቀ

44፥22 ፦ ሮም 8፥36። 45፥6-7 ፦ ዕብ. 1፥8-9።

ኅጠኛ ልብስ ተጐናጽፋ ፥
ከዙፋንህ በስተቀኝ ቆማለች ።

[10] አንቺ ልጂ ሆይ!
የምልሽን ስሚ ፤ ቃሌንም አድምጪ ፤
ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ ።
[11] በውበትሽ ንጉሡ ይወድድሻል ፤
ሆኖም ጌታሽ በመሆኑ ታዘዥው ።
[12] የጢሮስ ሕዝብ ስጦታ ያመጡልሻል ፤
ሀብታሞችም ደጅ ይጠኑሻል ።
[13] በቤተ መንግሥት የተቀመጠችው ልዕልት
እንዴት ታምራለች!
ልብስዋም በወርቅ ያሸበረቀ ነው ።
[14] ኅጠኛ ልብስዋንም ተጐናጽፋ
ወደ ንጉሡ ትቀርባለች ፤
ሚዜዎችዋ የሆኑ ልጃገረዶችም
ያጅቡአታል ፤
[15] በደስታና በሐሤትም
አብረው ወደ ንጉሡ ቤት ይገባሉ ።

[16] ንጉሥ ሆይ!
በቀድሞ አባቶችህ ተተክተው
የሚነግሡ
ብዙ ልጆች ይኖሩሃል ፤
አንተም በምድር ሁሉ ላይ
ትሾማቸዋለህ ።
[17] እኔም በዘመናት ሁሉ ዝናህን በቅኔ
እናገራለሁ ፤
ሕዝቦችም ሁሉ ለዘላለም
ያመሰግኑሃል ።

## ምዕራፍ 46

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው

[1] እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኀይላችን
ነው ፤
ችግር በሚደርስብን ጊዜ ሁሉ
ረዳታችን ነው ።
[2] ስለዚህ ምድር ብትናወጥ ፥
ተራራዎች ወደ ጥልቅ ባሕር
ቢወድቁ ፥
[3] ባሕሮች ታውከው ድምፃቸውን
ቢያሰሙ ፥
በእነርሱም የእንቅስቃሴ ኀይል
ተራራዎች ቢንቀጠቀጡ አንፈራም ።

[4] የእግዚአብሔርን ከተማ ፥
የተቀደሰችውን የልዑል መኖሪያ ፥
የሚያረካና ደስ የሚያሰኝ ወንዝ አለ ።
[5] እግዚአብሔር ከእርስዋ ጋር ስለሆነ
ያች ከተማ አትናወጥም ፤
ጠዋት በማለዳ እግዚአብሔር ፈጥኖ
ይረዳታል ።

[6] ሕዝቦች ተሸበሩ ፤
ነገሥታትም ወደቁ ፤
እግዚአብሔር የቍጣ ድምፁን ባሰማ
ጊዜ ፥
ምድር ቀለጠች ።

[7] ሁሉን የሚችል አምላክ ከእኛ ጋር ነው ፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው ።

[8] ኑ ፥ የእግዚአብሔርን ሥራ እዩ!
በምድር ላይ ያደረገውን አስገራሚ
ነገር ተመልከቱ!
[9] እርሱ በመላው ዓለም የሚካሄደውን
ጦርነት ሁሉ ያቆማል ፤
ቀስትን ይሰብራል ፤ ጦርነትንም
ያደቅቃል ፤
ጋሻንም በእሳት ያቃጥላል ።
[10] እርሱ “ውጊያን ሁሉ አቁማችሁ ጸጥ
በማለት
እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ዕወቁ ፤
እኔ ከሕዝቦች ሁሉ በላይ ነኝ”
ይላል ።
[11] ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር
ነው ፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው ።

## ምዕራፍ 47

እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ንጉሥ ነው

[1] ሕዝቦች ሆይ! በደስታ አጨብጭቡ ፤
ከፍ ባለ ድምፅ በመዘመር ፥
እግዚአብሔርን አመስግኑ ።
[2] ዓለምን የሚገዛ ታላቅ ንጉሥ ስለሆነ
ልዑል እግዚአብሔር መፈራት
ይገባዋል ።
[3] እርሱ ሕዝቦች ጸጥ ብለው
እንዲገዙልንና ፥
መንግሥታትም በቍጥጥራችን ሥር
እንዲሆኑ አደረገ ።
[4] እርሱ የምንወርሳትን ምድር መረጠልን ፤
ይህችም ምድር ለሚወድደው
ለእስራኤል ሕዝብ መመኪያ ናት ።

[5] አምላክ ወደ ላይ ወደ ዙፋኑ ወጣ ፤
እግዚአብሔር ወደ ላይ በሚወጣበት
ጊዜ
የእልልታና የመለከት ድምፅ ተሰማ ።
[6] የምስጋና መዝሙር ለአምላካችን ዘምሩ ፤
የምስጋና መዝሙር ለንጉሣችን
አቅርቡ ።
[7] አምላካችን የዓለም ሁሉ ንጉሥ ነው ፤
ስለዚህ የምስጋና መዝሙር
ዘምሩለት ።

10 ማንም እንደሚያውቀው ፥
ጠቢባን እንኳ ከሞኞችና ከሰነፎች
እኩል ይሞታሉ ፤
ሁሉም ሀብታቸውን ትተው ይሄዳሉ ።
11 ምንም እንኳ “የብዙ መሬት
ባለንብረቶች ነን”
ብለው ቢመኩም ፥
እርሱን ለሌሎች ትተው በመቃብር
ይኖራሉ ፤
መቃብርም ለዘላለም ቤታቸው
ይሆናል ።
12 ሰውን ገናናነቱ ከሞት አያድነውም ፤
የቱንም ያህል ዝነኛ ቢሆን
እንደ እንስሳ መሞቱ አይቀርም ።
13 በራሳቸው የሚመኩና የሀብታቸው
ተካፋዮች በመሆን ፥
ቃላቸውን የሚያደንቁ ተከታዮቻቸው
ሁሉ ምን እንደሚደርስባቸው
እዩ ፤
14 እነርሱ ዕድል ፈንታቸው
እንደ በግ ወደ መታረድ መነዳት
ነው ፤
ሞትም እንደ እረኛ ሆኖ
ይጠብቃቸዋል ፤
ሥጋቸውም ከክብር መኖሪያው ርቆ
በመቃብር ውስጥ ይበሰብሳል ፤
ደጋግ ሰዎችም በማለዳ ተነሥተው
በእነርሱ ላይ ሥልጣናቸውን ያሳያሉ ።
15 እኔንም እግዚአብሔር ይታደገኛል ፤
ከሞትም ኀይል ያድነኛል ።

16 ሰው ሀብታም ሲሆን ፥
የቤቱም ብልጽግና እየበዛ ሲሄድ ፥
አትፍራው ፤
17 ምክንያቱም በሚሞትበት ጊዜ ምንም
ነገር አይወስድም ፤
ሀብቱም ከእርሱ ጋር ወደ መቃብር
አይወርድም ።
18 ሰው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ቢደሰትና
ሁሉም ነገር ስለተሳካለት ቢመሰገንም
እንኳ ፥
19 በሞት ተለይቶ ዳግመኛ ብርሃንን
ወደማያይበት
ወደ ቀድሞ አባቶቹ ይሄዳል ።
20 ያለ ማስተዋል ሀብት ያካበተ ሰው
እንደ እንስሳ መሞቱ አይቀርም ።

## ምዕራፍ 50
### እውነተኛ አምልኮ

1 ሁሉን ቻይ የሆነ እግዚአብሔር አምላክ
ይናገራል ፤
ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያሉትንም
የዓለም ሕዝቦች ይጠራል ።
2 እግዚአብሔር በውበትዋ ፍጹም
ከሆነችው
ከጽዮን ከተማ ያበራል ።

3 አምላካችን ይመጣል ፤ ዝም አይልም ፤
የሚያቃጥል እሳት በፊቱ ነው ፤
ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው
ነው ።
4 በሕዝቡ ላይ ሲፈርድ ፥
ሰማይንና ምድርን ለምስክርነት
ይጠራል ።
5 ከዚህም በኋላ “መሥዋዕት በማቅረብ
ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን የገቡትን ፥
ታማኞች የሆኑትን ወገኖቼን ወደ እኔ
ሰብስቡ !” ይላል ።
6 እግዚአብሔር ራሱ እውነተኛ ፈራጅ
መሆኑን
ሰማያት ይመሰክራሉ ።

7 ቀጥሎም እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤
“ሕዝቤ ሆይ ! ቃሌን ስማ ፤
እስራኤል ሆይ ! በአንተ
እመሰክራለሁ ፤
እኔ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ ።
8 ስለ መሥዋዕትህና ዘወትር
ስለምታቀርበው
የሚያቃጥል መባ አልወቅስህም ።
9 እንዲሁም ከበረትህ ኮርማዎችን ፥
ከጕሮኖህ አውራ ፍየሎችን
ልወስድብህ አልፈልግም ።
10 በዱር ያሉ አራዊትና
በሺ የሚቈጠሩ ተራራዎች ላይ
የሚሠማሩት
የእንስሳት መንጋዎች የእኔ ናቸው ።
11 የበረሓ ወፎችና በዱር የሚኖሩ
ሕያው ፍጥረቶች ሁሉ የእኔ ናቸው ።

12 “ቢርበኝ እንኳ ለአንተ አልነግርህም ፤
ምክንያቱም ዓለምና በውስጥዋ ያለው
ነገር ሁሉ የእኔ ነው ።
13 እኔ እኮ የኮርማዎችን ሥጋ አልበላም ፤
የፍየሎችንም ደም አልጠጣም ።
14 ስለዚህ ምስጋናን መሥዋዕት አድርገህ
ለእግዚአብሔር አቅርብ ፤
ስእለትህንም ለልዑል እግዚአብሔር
ስጥ ።
15 መከራ በሚደርስብህ ጊዜ ጥራኝ ፤
እኔም አድንሃለሁ ፤
አንተም ታከብረኛለህ ።”

16 ኃጢአተኛውን ግን እግዚአብሔር እንዲህ
ይለዋል ፥
“ሕጌን በማነብነብ ለምን ትናገራለህ?
ስለ ቃል ኪዳኔስ ለምን ታወራለህ?

## ምዕራፍ 52

የእግዚአብሔር ፍርድና የእግዚአብሔር ጸጋ

1 አንተ ብርቱ ሰው!
በእግዚአብሔር ወገኖች ላይ ክፉ ነገር
በማድረግ
ስለምን ዘወትር ትመካለህ?
የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ መሆኑን
እያወቅህስ፣
2 ሌሎችን ለማጥፋት ለምን ታስባለህ?
አንደበትህ እንደ ተሳለ ምላጭ ነው፤
ዘወትር የሐሰትን ነገር
ታውጠነጥናለህ።
3 ከደግነት ይልቅ ክፋትን፣
ከእውነት ይልቅ ሐሰትን
ትመርጣለህ።
4 አንተ ሐሰተኛ ሰው!
ሰዎችን የሚጐዳ ቃል መናገር
ትወድዳለህ።

5 ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለሙ
ያጠፋሃል፤
ከቤትህ አስወጥቶ ያባርርሃል።
ከሕያዋንም ምድር ያስወግድሃል።
6 የእግዚአብሔር ሰዎችም ይህን አይተው
ይፈራሉ፤
በአንተም ላይ እየሳቁ፣
7 "በእግዚአብሔር በመተማመን
ዋስትናን ለማግኘት ያልፈለገ ሰው
ይኸውላችሁ!
እርሱ የሚተማመነው በሀብቱ ብዛት
ነው፤
ዋስትናው ያደረገውም ክፋት
መሥራትን ነው" ይላሉ።
8 እኔ ግን በእግዚአብሔር ቤት፣
እንደ ለምለም የወይራ ዛፍ ነኝ፤
በማያቋርጥ ፍቅሩም፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም እታመናለሁ።
9 አምላክ ሆይ!
ስላደረግኸው መልካም ነገር ሁሉ
አመሰግንሃለሁ፤
በደጋግ ሰዎች ፊት ቆሜ ስለ አንተ
ቸርነት
እናገራለሁ።

## ምዕራፍ 53

የሰዎች ክፋት

(የመዝሙር 14 ተመሳሳይ)

1 ሞኞች በልባቸው፣
"እግዚአብሔር የለም" ይላሉ፤
ሕይወታቸው ተበላሽቶአል፤
አጸያፊ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ፤
ከመካከላቸው አንድ እንኳ
መልካም ሥራ የሚሠራ የለም፤

2 እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ጥበበኞች
ይገኙ እንደሆን ለማየት፣
እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ሰዎችን
ተመለከተ።
3 ነገር ግን ሁሉም ዐምፀዋል፤
ልዩነት ሳይኖራቸው፣
ሁሉም በአንድነት ረክሰዋል፤
ከእነርሱ አንድ እንኳ
መልካም ነገርን የሚያደርግ የለም።

4 እግዚአብሔር "እነዚህ ክፉ አድራጊዎች
ምንም የማያውቁ ሞኞች ናቸው፤
ሕዝቤን በመበዝበዝ ይኖራሉ እንጂ
ወደ እኔ አይጸልዩም" ይላል።

5 እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች
ስለሰባበራቸው፣
ከምንጊዜውም ይልቅ በፍርሃት
ተጨነቁ፤
እግዚአብሔርም ስለጣላቸው ፈጽሞ
ያፍራሉ።

6 ለእስራኤል ደኅንነትን ከጽዮን ማን
በሰጠ?
እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ
በሚመልስበት ጊዜ፣
የያዕቆብ ልጆች ደስ ይላቸዋል፤
የእስራኤል ሕዝብ ሐሴት ያደርጋል።

## ምዕራፍ 54

ከጠላት እጅ ለመዳን የቀረበ ጸሎት

1 አምላክ ሆይ! በስምህ አድነኝ፤
በኀይልህም ነፃ አውጣኝ።
2 አምላክ ሆይ! ጸሎቴን ስማ፤
ቃሌንም አድምጥ።
3 ለእግዚአብሔር ደንታ የሌላቸው
ትዕቢተኞች ሊያጠቁኝ መጥተዋል፤
ጨካኞች ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ።

4 ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ
የእኔ ረዳትና የእኔ ተከላካይ ነው።
5 እግዚአብሔር ጠላቶቼን
በገዛ ክፋታቸው ይቀጣቸዋል፤
እውነተኛ ስለሆነም ፈጽሞ
ያጠፋቸዋል።

52፥1-9 ፡- 1ሳሙ. 22፥9-10። 53፥1-3 ፡- ሮም 3፥10-12። 54፥1-7 ፡- 1ሳሙ. 23፥19፤ 26፥1።

በእኔ ላይ በጠላትነት የተነሡትም
እጅግ ብዙ ናቸው ።
3 ሁሉን ቻይ የሆንህ እግዚአብሔር ሆይ!
ፍርሃት ቢይዘኝ እንኳ ፥
በአንተ እተማመናለሁ ።
4 በእግዚአብሔር ስለምታመን አልፈራም ፤
ስለ ሰጠኝም ተስፋ አመሰግነዋለሁ ፤
በእግዚአብሔር ስለምታመን
ከቶ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?

5 ጠላቶቼ በየቀኑ ችግር ይፈጥሩብኛል ፤
ዘወትር እኔን ለመጕዳት ያቅዳሉ ።
6 በስዋራ ቦታዎች ይሰበሰባሉ ፤
ሊገድሉኝም ስለሚፈልጉ ፥
እየተከታተሉ የማደርገውን ሁሉ
ይመለከታሉ ።
7 አምላክ ሆይ!
በክፉ ሥራቸው ቅጣቸው ፤
በቍጣህ አረማውያንን አዋርዳቸው ።

8 ሁሉም በመዝገብህ የሰፈረ ስለሆነ
ምን ያህል እንደተቸገርሁና ፥
ምን ያህል እንባ እንደፈሰሰኝም አንተ
ታውቃለህ ።
9 እኔ ወደ አንተ በምጣራበት ቀን ፥
ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ ፤
እግዚአብሔር ከእኔ ጋር መሆኑንም
በዚህ ዐውቃለሁ ።
10 ይህም ከእኔ ጋር የሆነው እግዚአብሔር ፥
ቃሉን የማመሰግነውና የማከብረው
አምላክ ነው ።
11 በእርሱም ስለምታመን አልፈራም ፤
ሰውስ ከቶ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?

12 አምላክ ሆይ!
ለአንተ የተሳልሁትን እፈጽማለሁ ፤
ምስጋናንም መሥዋዕት አድርጌ
አቀርብልሃለሁ ።
13 አንተ ከሞት አድነኸኛል ፤
ተሰናክዬ እንዳልወድቅም
ረድተኸኛል ፤
ስለዚህ በሕያዋን ላይ በሚያበራው
ብርሃን
በእግዚአብሔር ፊት እመላለሳለሁ ።

## ምዕራፍ 57

### የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

1 አምላክ ሆይ!
ሰላምን ለማግኘት አንተን መጠጊያ
አድርጌአለሁና
ጌታ ሆይ! ማረኝ ፤
እስፈሪ ሞገድ እስከሚያልፍ
በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያ
አገኛለሁ ።

2 የሚያስፈልገኝን ሁሉ ወደሚሰጠኝ
ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጣራለሁ ።
3 እርሱም ከሰማይ ሰምቶ ያድነኛል ፤
የሚያስጨንቁኝንም ያዋርዳቸዋል ፤
እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅሩንና
እውነተኛነቱን ያሳየኛል ።

4 ሰው እንደሚበሉ አንበሶች የሆኑ ጠላቶቼ
ከብበውኛል ፤
ጥርሳቸው እንደ ጦርና እንደ ፍላጻ
ነው ፤
ምላሳቸው እንደ ተሳለ ሰይፍ ነው ።

5 አምላክ ሆይ!
ታላቅነትህን በሰማይ ግለጥ ፤
ክብርህንም በምድር ላይ አሳይ ።

6 ጠላቶቼ እኔን ለመያዝ ወጥመድ
ዘርግተውብኛል ፤
ሁለንተናዬን የሚያጕብጥ ተስፋ
መቍረጥ ደረሰብኝ ፤
በመንገዴ ጕድጓድ ቈፈሩ ፤
ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው ገቡበት ።

7 አምላክ ሆይ! በሙሉ ልቤ
እተማመናለሁ ፥
ስለዚህ በዝማሬ አመሰግናለሁ ።
8 ነፍሴ ሆይ! ተነሺ!
በገናዬና መሰንቆዬም ተነሡ!
እኔም በማለዳ እነሣለሁ ።
9 እግዚአብሔር ሆይ!
በመንግሥታት መካከል
አመሰግንሃለሁ ፤
በሕዝቦችም መካከል የምስጋና
መዝሙር አቀርብልሃለሁ ።
10 ዘላለማዊው ፍቅርህ ከሰማያት በላይ
ነው ፤
እውነተኛነትህም ከጠፈር በላይ
የሚደርስ ነው ።
11 አምላክ ሆይ!
ታላቅነትህን ከሰማያት በላይ ግለጥ ፤
ክብርህንም በምድር ሁሉ ላይ አሳይ ።

## ምዕራፍ 58

### እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን እንዲቀጣ የቀረበ ጸሎት

1 እናንተ ገዢዎች!
ትክክለኛ ፍትሕ ትሰጣላችሁን?

57፥1-11 ፦ 1ሳሙ. 22፥1 ፤ 24፥3 ።

⁷ አምላክ ሆይ!
በፊትህ ለዘላለም እንዲነግሥ
አድርገው፤
በዘላለማዊው ፍቅርህና
በእውነተኛነትህ ጠብቀው።

⁸ ለአንተ የተሳልሁትን በየቀኑ በማቅረብ
ዘወትር የምስጋና መዝሙር
እዘምርልሃለሁ።

## ምዕራፍ 62
በእግዚአብሔር ጠባቂነት መተማመን

¹ የሚያድነኝ እርሱ ብቻ ስለሆነ፥
እግዚአብሔርን በትዕግሥት
እጠባበቃለሁ።
² ያለ እርሱ የሚጠብቀኝና የሚያድነኝ
የለም፤
መከላከያዬም እርሱ ስለሆነ ከቶ
አልናወጥም።

³ እንደ ዘመመ ግድግዳና እንደ ወደቀ
ቅጽር
አቅም ያነሰውን ሰው፥
እስከ መቼ ስታጠቁት ትኖራላችሁ?
⁴ እናንተ የምትፈልጉት ከብሩን ለመሻር
ስለሆነ፥
በእርሱ ላይ ሐሰት መናገርን
ትወድዳላችሁ፤
በአፋችሁ ትመርቁታላችሁ፤
በልባችሁ ግን ትረግሙታላችሁ።

⁵ እኔ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ
እደገፋለሁ፤
የመዳን ተስፋዬንም በእርሱ ላይ
አደርጋለሁ።
⁶ ከእርሱ በቀር ሌላ የሚጠብቀኝና
የሚያድነኝ የለም፤
መከላከያዬም እርሱ ስለሆነ ከቶ
አልናወጥም።
⁷ ደኅንነቴና ክብሬ የተገኘው
ከእግዚአብሔር ነው፤
እርሱ ብርቱ ጠባቂዬና መከታዬ ነው።

⁸ ሕዝቦች ሆይ!
ዘወትር በእግዚአብሔር ታመኑ፤
እርሱ መጠጊያችን ስለሆነ
ችግራችሁን ሁሉ ለእርሱ ንገሩት።

⁹ ሰዎች ሁሉ ተንኖ እንደሚጠፋ ትንፋሽ
ናቸው፤
ታናናሾችም ሆኑ ታላላቆች፥ ሁሉም
ከንቱ ናቸው፤
በሚዛን ቢመዘኑ፥ ምንም ክብደት
የላቸውም፤
ከትንፋሽ እንኳ የቀለሉ ናቸው።
¹⁰ በብዝበዛ አትመኩ፤
በቀማችሁትም ነገር ለመክበር ተስፋ
አታድርጉ፤
ሀብታችሁ ቢበዛ እንኳ በእርሱ
አትተማመኑ።

¹¹ እግዚአብሔር "ኀይል የእኔ ነው!"
ብሎ ሲናገር፥ ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ።
¹² ፍቅሩም የማያቋርጥ መሆኑን
ዐውቃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ ራስህ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው
መጠን ዋጋውን ትከፍለዋለህ።

## ምዕራፍ 63
እግዚአብሔርን መፈለግ

¹ እግዚአብሔር ሆይ! አንተ አምላኬ ነህ፤
አንተን ለማግኘት በብርቱ
እናፍቃለሁ፤
ሁለንተናዬ አንተን ይመኛል፤
ውሃ በማጣት ደርቆ እንደተሰነጣጠቀ
መሬት
ነፍሴ አንተን ተጠማች።
² በመቅደስህ ውስጥ እንዳይህ ፍቀድልኝ፤
ኀይልህንና ክብርህንም አሳየኝ።
³ ዘላለማዊው ፍቅርህ ከሕይወት እንኳ
የሚሻል ስለሆነ አመሰግንሃለሁ።
⁴ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ አመሰግንሃለሁ፤
ስጸልይም እጆቼን ወደ አንተ
እዘረጋለሁ።
⁵ ሰው መልካም ምግብ በልቶ
እንደሚጠግብ
ነፍሴ በአንተ ትረካለች፤
ስለዚህ የምስጋና መዝሙር በደስታ
እዘምርልሃለሁ።

⁶ በመኝታዬም ሆኜ አስታውስሃለሁ፤
ሌሊቱንም ሁሉ የአንተን ነገር
አስባለሁ።
⁷ አንተ ረዳት ስለሆንከኝ በክንፎችህ ሥር
ተጠልዬ፥
በደስታ እዘምራለሁ።
⁸ ወደ አንተ እጠጋለሁ፤
ቀኝ እጅህም በሰላም ይጠብቀኛል።

62፥12 ፦ ኢዮብ 34፥11፤ ኤር. 17፥10፤ ማቴ. 16፥27፤ ሮም 2፥6፤ ራእ. 2፥23። 63፥1-11 ፦ 1ሳሙ. 23፥14።

9 እኔን ለመግደል የሚፈልጉ ሁሉ ፥
ወደ ሙታን ዓለም ይወርዳሉ ።
10 በሰይፍ ይገደላሉ ፤
ሬሳቸውንም ቀበሮዎች ይበሉታል ።
11 እግዚአብሔር ድልን ስለሚያጐናጽፈው
ንጉሡ ደስ ይለዋል ፤
በእግዚአብሔር ስም ቃል ኪዳን የሚገቡ
ሁሉ ፥
እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ፤
የሐሰተኞች አንደበት ግን ይዘጋል ።

## ምዕራፍ 64
### የመማጸኛ ጸሎት

1 አምላክ ሆይ !
ተጨንቄአለሁና ጸሎቴን ስማኝ ፤
ጠላቶቼን ፈርቻቸዋለሁና ሕይወቴን
አድን ።
2 ተሰብስበው በመጮኽ ፥ ክፉ ሥራ
ከሚያደርጉ ፥
ከጨካኞች ሤራ ሰውረኝ ።
3 እነርሱ ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ
ይስላሉ ፤
እጅግ የከፉ ቃላትን እንደ ፍላጻ
አነጣጥረው ይወረውራሉ ።
4 የሐሰት ወሬን በንጹሕ ሰው ላይ
ያሰራጫሉ ፤
የመልካም ሰዎችንም ስም በሐሜት
ያጠፋሉ ።
5 ክፉ ሤራ ለማቀነባበር እርስ በርሳቸው
ይመካከራሉ ፤
ወጥመዳቸውንም የት እንደሚዘረጉ
ያቅዳሉ ፤
ይህን ሁሉ ሲያደርጉ “ማንም ሊያየን
አይችልም !” ይላሉ ።
6 የዐመፅ ዕቅድ ካወጡ በኋላ
“እንግዲህ ፍጹም የሆነ የዐመፅ ዕቅድ
አውጥተናል” ይላሉ ።
ይህም የሰው ልብና የሰው አእምሮ
በተንኰል
የተሞላ መሆኑን ያሳያል ።

7 እግዚአብሔር ግን ፍላጻዎችን
ወደ እነርሱ ይወረውራል ፤
እነርሱም በድንገት ይቈስላሉ ።
8 በእብሪት ንግግራቸው ምክንያት
ያጠፋቸዋል ፤
የሚያዩአቸውም ሁሉ በመገረም
ራሳቸውን ይነቀንቃሉ ።
9 ሁሉም ይፈራሉ ፤
እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር
ያሰላስላሉ ፤
ስለ ሥራውም ሁሉ ያወራሉ ።
10 እግዚአብሔር ስላደረገው ድንቅ ነገር
ደጋግ ሰዎች ሁሉ ደስ ይላቸዋል ፤
በእርሱም ሰላም ያገኛሉ ፤
ልበ ቅኖችም ያመሰግኑታል ።

## ምዕራፍ 65
### ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ማቅረብ

1 አምላክ ሆይ !
በጽዮን ሆነን አንተን ማመስገን ፤
ለአንተ የተሳልነውንም መስጠት
ይገባናል ።
2 አንተ የሰዎችን ጸሎት ስለምትሰማ
ሰዎች ሁሉ ወደ አንተ ይመጣሉ ።
3 ኃጢአት በላያችን በርትቶብን ነበር ፤
አንተ ግን በደላችንን ሁሉ ይቅር
አልከልን ።
4 አንተ የመረጥሃቸውና በተቀደሰ
አደባባይህ
እንዲኖሩ ወደ ራስህ ያቀረብሃቸው ፥
ደስ ይበላቸው ፤
እኛም ከቤትህ በሚገኘው መልካም
ነገርና
ከመቅደስህ በሚገኘው በረከት
እንረካለን ።

5 ጸሎታችንን ሰምተህ ድልን
ታጐናጽፈናለህ ፤
እኛንም ለማዳን ብዙ ድንቅ ነገሮችን
ታደርጋለህ ፤
ሩቅ ከሆነው ባሕር ማዶ ያሉት ሳይቀሩ
የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በአንተ
ይታመናሉ ።
6 ተራራዎችን በየስፍራቸው አጽንተህ
በማኖርህ
ብርቱ ኀይልህን አሳይተሃል ።
7 ከባሕሩ መናወጥ የተነሣ
የማያስገመግመውን
የማዕበል ድምፅ ጸጥ ታደርጋለህ ፤
የሕዝቦችንም የድንፋታ ድምፅ ዝም
ታሰኛለህ ።
8 ስላደረግሃቸው ተአምራት ፥
ዓለም በሙሉ በፍርሃት ይጨነቃል ።
በአንተ ድንቅ ሥራ ምክንያት ፥
ከምድር ዳርቻ እስከ ምድር ዳርቻ
የእልልታ ድምፅ ይሰማል ።

9 ዝናምን በማዝነም ምድርን ትጐበኛለህ ፤
ፍሬያማ በማድረግ ታበለጽጋታለህ ፤
ምንጮችን በውሃ ትሞላለህ ፤
ለምድርም ሰብልን ትሰጣለህ ።
ይህንንም የምታደርገው እንዲህ ነው ፥

16 ታዲያ የሰልሞን ተራራ በታላላቅ ጫፎቹ
ተመክቶ፥
እግዚአብሔር መኖሪያው ለማድረግ
የመረጠውን ተራራ ስለምን በንቀት
ይመለከታል?
በዚያ እኮ እግዚአብሔር ለዘላለም
ይኖርበታል።
17 እግዚአብሔር በብዙ ሺ ከሚቈጠሩት
ታላላቅ ሠረገላዎች ጋር ከሲና ወደ
ተቀደሰው ስፍራ ይመጣል።
18 ብዙ ምርኮ ከማረከም በኋላ
ወደ ከፍታዎች ይወጣል፤
በመፀኞች እንኳ ሳይቀሩ፥ ሰዎች ሁሉ
መባ ያመጡለታል፤[3*]
እግዚአብሔር አምላክም በዚያ ይኖራል።
19 ሸክማችንን በየቀኑ የሚያቀልልንና እኛን
የሚያድን
እግዚአብሔር አምላክ የተመሰገነ
ይሁን።
20 አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው፤
ከሞት የሚታደገን አምላክ፥
እግዚአብሔር ነው።
21 በእርግጥ እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ
ይቀጠቅጣል፤
በኃጢአት የጸኑትንም ሰዎች አናት
ይሰባብራል።
22 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥
ጠላቶችህን ከባሳንና ከጥልቅ ባሕር
መልሼ አመጣቸዋለሁ።
23 አንተም ደማቸውን ረግጠህ ታልፋለህ፤
ውሾችህም እስከሚጠግቡ ደም
ይልሳሉ።"

24 አምላክ ሆይ!
የድል አድራጊነትህ ሰልፍ በሁሉም
ይታያል፤
የእኔ ንጉሥ የሆነው አምላክ በክብር
አጀብ ወደ መቅደሱ
ሲገባ ይታያል።
25 ዘማሪዎች ከፊት፥ ሙዚቀኞች ከኋላ፥
አታሞ የሚመቱ ልጃገረዶች
ከመካከል፥
ሆነው ይታያሉ።
26 እነርሱም "በሕዝቡ ጉባኤ መካከል
አምላክን አመስግኑ፤
የእስራኤል ተወላጆች የሆናችሁ ሁሉ
እግዚአብሔርን አመስግኑ" ይላሉ።
27 በመጀመሪያ ከሁሉ ታናሽ የሆነው
የብንያም ነገድ ታየ፤
ቀጥሎም የይሁዳ መሪዎች
ከነጭፍሮቻቸው ታዩ።
በመጨረሻም የዛብሎንና የንፍታሌም
መሪዎች ተከተሉ።

28 አምላክ ሆይ! ኀይልህን ግለጥ!
ከዚህ በፊት እኛን ያዳንህበትን
ብርታትህን አሳይ!
29 በዚህ ዐይነት በኢየሩሳሌም ስላለው
መቅደስህ
ነገሥታት መባን ያመጡልሃል።
30 እንደ አውሬ በሸንበቆዎች ውስጥ
የምትኖረውን ግብጽን ገሥጽ!
ኮርማዎችና ጥጆች የመሳሰሉትን
መንግሥታት ገሥጻቸው!
ሁሉም ተንበርክከው ብራቸውን
እስኪያቀርቡልህ ድረስ ገሥጻቸው!
ጦርነት ማድረግ የሚፈልጉትንም
ሕዝቦች በትናቸው!
31 የሰላም መልክተኞች ከግብጽ ይመጣሉ፤
ኢትዮጵያም ፈጥና እጆችዋን
ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።

32 የዓለም መንግሥታት ሁሉ ለአምላክ
ዘምሩ፤
ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር
አቅርቡ።
33 ከሰማያት በላይ ወዳለው ሰማይ
ለሚመጣው ዘምሩ፤
በሚያስገመግም ብርቱ ድምፅ
ሲናገርም አድምጡት።
34 የእምላክን ኀይል ዐውጁ፤
ምክንያቱም ግርማው በእስራኤል፥
ኀይሉም በሰማይ ላይ ነው።
35 የእስራኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር፥
ከመቅደሱ በሚገለጥበት ጊዜ እጅግ
ያስፈራል፤
እርሱ ለሕዝቡ ብርታትንና ኀይልን
ይሰጣል።

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

## ምዕራፍ 69

### ዕርዳታ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

1 የውሃ ሙላት እስከ አንገቴ ስለደረሰ፤
አምላክ ሆይ! አድነኝ፤
2 መቆሚያ ስፍራ ስላጣሁ በጥልቅ ረግረግ
ውስጥ
ለመስጠም ተቃርቤአለሁ፤

---

3* 68፥18 ሰዎች ሁሉ መባ ያመጡለታል ፦ ወይም "ለሰዎች ስጦታዎችን ሰጠ" (ኤፌ. 4፥8 ተመልከት)።
68፥18 ፦ ኤፌ. 4፥8።

በጥልቅ ውሃ ውስጥ እገኛለሁ ፤
ማዕበልም ሊያሰጥመኝ ተቃርቦአል ።
3 ዕርዳታ ለማግኘት ወደ አንተ ከመጮኼ ብዛት የተነሣ ደክምሁ ፤
ጕሮሮዬም ቈሰለ ፤
አንተን በመጠባበቅ ዐይኖቼ ፈዘዙ ።

4 ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ ከራሴ ጠጕር ይልቅ በዝተዋል ፤
ጠላቶቼ በእኔ ላይ ሐሰት ይናገራሉ ፤
ብርቱዎች ስለሆኑም ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ ፤
ያልሰረቅሁትን ነገር እንድክፍል ያስገድዱኛል ።
5 አምላክ ሆይ!
ኃጢአቴ ከአንተ የተሰወረ አይደለም ፤
ምን ያህል አስነዋሪ እንደሆንሁም አንተ ታውቃለህ ።
6 የሠራዊት ጌታ የሆንህ አምላክ ሆይ!
በአንተ በሚታመኑት ላይ ሐፍረት እንዳላመጣባቸው ጠብቀኝ ፤
የእስራኤል አምላክ ሆይ!
አንተን የሚያገለግሉ ሁሉ በእኔ ምክንያት ውርደት እንዳይደርስባቸው ጠብቀኝ ።
7 አንተን በማገልገል ብዙ ስድብ ደርሶብኛል ፤
ሐፍረትም ፊቴን ሸፍኖታል ።
8 በወንድሞቼ መካከል እንደ እንግዳ ተቈጠርሁ ፤
በቤተሰቤም መካከል እንደ ባይተዋር ሆንሁ ።

9 ለቤትህ ያለኝ መንፈሳዊ ቅንአት በውስጤ እንደ እሳት ይነድዳል ፤
በአንተ ላይ የተሰነዘረው ስድብ በእኔ ላይ ዐረፈ ።
10 ሰውነቴን በጾም ሳዋርድ ሰዎች ይሰድቡኛል ።
11 የሐዘን ልብስ ስለብስ እየተዘባበቱ ይስቁብኛል ።
12 በየመንገዱ የሚያወሩት ስለ እኔ ነው ፤
ሰካራሞች በዘፈን ይሰድቡኛል ።

13 እግዚአብሔር ሆይ!
እኔ ግን ወደ አንተ እጸልያለሁ ፤
አምላክ ሆይ! ለማዳን የሰጠኸውን ተስፋ የምትፈጽም ስለሆንህ ፥
አንተ በመረጥኸው ጊዜ የጸሎቴን መልስ ስጠኝ ፤
ስለ ታላቁ ፍቅርህም ስማኝ ።
14 በረግረግ ውስጥ ከመስጠም አድነኝ ፤
ከጠላቶቼም ጠብቀኝ ፤
በጥልቅ ውሃም ከመስጠም ሰውረኝ ።
15 ጐርፍ እንዳይወስደኝ ፥
ጥልቅ ባሕር እንዳያስጥመኝ ፥
መቃብር እንዳይውጠኝ ጠብቀኝ ።

16 እግዚአብሔር ሆይ!
ቸርነት በተሞላበት ፍቅርህ ጸሎቴን ስማ ፤
በታላቁ ምሕረትህ ወደ እኔ ተመለስ ።
17 ከእኔ ከአገልጋይህ አትሰወር ፤
በከባድ ጭንቅ ላይ ስለሆንሁ ፥
ፈጥነህ ስማኝ ።
18 ወደ እኔ ቀርበህ አድነኝ ፤
ከጠላቶቼም ተቤዠኝ ።

19 ምን ያህል እንደምሰደብ አንተ ታውቃለህ ፤
ምን ይህል እንደተዋረድሁና ክብሬም እንደተቀነሰ ታስተውላለህ ፤
እነሆ ጠላቶቼ ሁሉ በፊትህ ናቸው ።
20 ስድብ ልቤን ስለሰበረው ተስፋ ቈረጥሁ ፤
የሚያስተዛዝነኝ ሰው ፈለግሁ ፤
ነገር ግን ማንም አልነበረም ፤
የሚያጽናናኝ ሰው ፈለግሁ ፤
ነገር ግን ማንም አልተገኘም ።
21 በምግቤ ውስጥ መራራ ነገር ቀላቀሉ ፤
በጠማኝም ጊዜ በውሃ ፈንታ ሆምጣጤ ሰጡኝ ።
22 በፊታቸው የተዘረጋው ማእድ ወጥመድ ይሁንባቸው ፤
በአምልኮ ጊዜ የሚመገቡትም ምግብ የመውደቂያቸውና
የመጥፊያቸው ምክንያት ይሁን ።
23 ዐይናቸው እንዳያይ ይጨልም ፤
ወገባቸው ሁልጊዜ ይንቀጥቀጥ ።
24 ቊጣህን በላያቸው አፍስስ ፤
የመዓትህም መቅሠፍት ይድረስባቸው ።
25 መኖሪያቸው ወና ይሁን ፤
በቤታቸው ውስጥ አንድም ሰው በሕይወት አይኑር ።
26 አንተ የቀጣሃቸውን ሰዎች ያሳድዳሉ ፤
አንተ ስላቈሰልሃቸውም ሰዎች መከራ ያወራሉ ።
27 ኃጢአታቸውን ሁሉ መዝግበህ ያዝ ፤
የደኅንነትህም ተካፋዮች አይሁኑ ።

69፥4 ፦ መዝ. 35፥19 ፤ ዮሐ. 15፥25 ። 69፥9 ፦ ዮሐ. 2፥7 ፤ ሮም 15፥3 ። 69፥21 ፦ ማቴ. 27፥48 ፤ ማር. 15፥36 ፤ ሉቃ. 23፥36 ፤ ዮሐ. 19፥28-29 ። 69፥22-23 ፦ ሮም 11፥9-10 ። 69፥25 ፦ ሐ.ሥ. 1፥20 ።

12 አምላክ ሆይ! ከእኔ አትራቅ ፤
አምላክ ሆይ! ፈጥነህ እርዳኝ ።
13 የሚያስጨንቁኝ ሁሉ ተሸንፈው ይጥፉ ፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ ሁሉ አፍረው
ይዋረዱ ።
14 ዘወትር አንተን ተስፋ አደርጋለሁ ፤
ባለማቋረጥም አመሰግንሃለሁ ።
15 ስለ ቅንነትህ ዘወትር እናገራለሁ ፤
ምንም እንኳ ለማስተዋል
ቢያዳግተኝም ፥
የአዳኝነትህን ሥራ በየቀኑ
እመሰክራለሁ ።
16 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ!
የሥራህን ታላቅነት እናገራለሁ ፤
አንተ ብቻ እውነተኛ እንደሆንህ
እመሰክራለሁ ።

17 አምላክ ሆይ!
አንተ ከልጅነቴ ጀምረህ
አስተማርኸኝ ፤
ገና አሁንም ድንቅ ሥራህን
እናገራለሁ ።
18 አምላክ ሆይ!
በእርጅናዬና ጠጉሬ ሽበት
በሚያወጣበት ጊዜ እንኳ
አትተወኝ ፤
ኀይልህንና ብርታትህን ለሚመጡት
ትውልዶች ሁሉ እስከገልጥ ድረስ
ከእኔ ጋር ሁን ።

19 አምላክ ሆይ!
ጽድቅህ እስከ ሰማይ ይደርሳል ፤
ታላላቅ ነገሮችን አድርገሃል ፤
አምላክ ሆይ! አንተን የሚመስል ማንም
የለም ።
20 በእኔ ላይ ብዙ ችግርና መከራ
አመጣህብኝ ፤
ነገር ግን ኀይሌን ታድሳለህ ፤
ወደ መቃብርም እንዳልወርድ
ትጠብቀኛለህ ።
21 ከምንጊዜውም ይልቅ ከፍ ከፍ
ታደርገኛለህ ፤
እንደገናም ፤ ታጽናናኛለህ ።

22 አምላኬ ሆይ!
ስለ እውነተኛነትህ በበገና
አመሰግንሃለሁ ፤
የእስራኤል ቅዱስ ሆይ!
በመሰንቆ የምስጋና መዝሙር
አቀርብልሃለሁ ።
23 በላዳንኸኝ የምሲጋና መዝሙር
አቀርብልሃለሁ ፤
ከደስታዬም ብዛት የተነሣ ድምፄን
ከፍ አድርጌ እዘምራለሁ ።
24 የሚያስጨንቁኝ ስለተሸነፉና
ስለተዋረዱ ፥
በየቀኑ ስለ ቅንነትህ እናገራለሁ ።

## ምዕራፍ 72

### ስለ ንጉሥ የቀረበ ጸሎት

1 አምላክ ሆይ!
ንጉሡ በአንተ ቅንነት እንዲፈርድ
አስተምረው ፤
የንጉሡም ልጅ ትክክለኛ ፍርድ
እንዲሰጥ እርዳው ።
2 በዚሁ ሁኔታ ሕዝብህን በቅንነት ፥
የተጨቈኑትንም በጽድቅ
ያስተዳድራል ።
3 ተራራዎች ብልጽግናን ፥ ኰረብቶችም
የጽድቅ ፍሬን ፤
ለሕዝብ ያስገኛሉ ።
4 ንጉሡ ለድኾች በቅንነት ይፈርዳል ፤
ችግረኞችንም ይረዳል ፤
የሚያስጨንቁአቸውንም
ያዋርዳቸዋል ።
5 ፀሐይ በሚወጣበት ዘመን ሁሉ ፥
ጨረቃም ብርሃንዋን በምትሰጥበት
ጊዜ ሁሉ ፥
ሕዝብህ ያገለግልሃል ።

6 ንጉሡ በመስክ ላይ እንደሚዘንም
ዝናም ፥
በምድርም ላይ እንደሚወርድ ካፊያ
ይሆናል ።
7 በእርሱ ዘመነ መንግሥት ቅኖች
ይከብራሉ ፤
ጨረቃ ብርሃንዋን በምትሰጥበት ጊዜ
ሁሉ ሰላም ይስፋፋል ።

8 ግዛቱ ከባሕር እስከ ባሕር ፥
ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ምድር ዳርቻ
ይደርሳል ።
9 በምድረ በዳ የሚኖሩ በፊቱ ይሰግዳሉ ፤
ጠላቶቹም ወደ መሬት ወድቀው
ትቢያ ይልሳሉ ።
10 የእስፔንና (የተርሴስ) የደሴቶች
ነገሥታት ስጦታ ያቀርቡለታል ፤
የሳባና የዐረብ ነገሥታት
እጅ መንሻ ያመጡለታል ።
11 ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል ፤
ሕዝቦች ሁሉ ያገለግሉታል ።

72፥8 ፦ ዘካ. 9፥10 ።

12 ወደ እርሱ የሚጮኹትን ድኾች ነፃ
ያወጣል ፤
ችግረኞችንና የተናቁትን ሰዎች
ይታደጋል ።
13 ለድኾችና ለደካሞች ይራራል ፤
በችግር ላይ ያሉትን ሰዎች ከሞት
ያድናል ።
14 የእነርሱ ሕይወት በእርሱ ዘንድ ውድ
ስለሆነ ፤
ከጭቈናና ከዐመፅ ይታደጋቸዋል ።

15 ንጉሡ ለዘላለም ይኑር ፤
ከዐረብ አገር ወርቅ ይምጣለት ፤
ስለ እርሱም ዘወትር ጸሎት ይደረግ ፤
የእግዚአብሔርም በረከት ዘወትር
ከእርሱ ጋር ይሁን ።
16 በምድሩ ላይ በቂ እህል ይኑር ፤
ተራራዎች በሰብል ይሸፈኑ ፤
እንደ ሊባኖስ ተራራዎችም ፍሬያማ
ይሁኑ ፤
ሜዳዎች በሣር እንደሚሸፈኑ ፤
ከተሞችም በሕዝብ ብዛት የተሞሉ
ይሁኑ ።
17 የንጉሡ ስም ለዘላለሙ ሲታወስ ይኑር ፤
ዝናውም ፀሐይ በሚወጣበት ዘመን
ሁሉ ይሰማል ፤
ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ምክንያት
ይባረካሉ ፤
ለእርሱም ደስታ እንዲሆን ይመኛሉ ።

18 ይህን ሁሉ ተአምራት የሚያደርግ እርሱ
ብቻ ስለሆነ ፤
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
የተመሰገነ ይሁን ።
19 ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን ፤
ክብሩ በምድር ሁሉ ይሙላ ፤

አሜን! አሜን!

20 የእሴይ ልጅ የዳዊት ጸሎት
እዚህ ላይ ተፈጸመ ።

## ክፍል ሦስት
(ከመዝሙር 73-89)

## ምዕራፍ 73
### የእግዚአብሔር ፍትሕ

1 ልባቸው ንጹሕ ለሆነ እስራኤላውያን
እግዚአብሔር እንዴት ቸር ነው!
2 እኔ ግን መተማመን ስለጐደለኝ ፤
እምነቴ ሊጠፋ ተቃርቦአል ፤
3 ምክንያቱም ትዕቢተኞችና ክፉ ሰዎች
ሁሉ ነገር ሲቃናላቸው በማየቴ ፤
በመቅናት ተበሳጭቼ ነበር ።
4 እነርሱ ብርቱዎችና ጤናማዎች ስለሆኑ ፤
ሕመምና ሥቃይ አይደርስባቸውም ።
5 እንደ ሌሎች ሰዎች አይጨነቁም ፤
በሌሎች ላይ የሚደርሰው ሥቃይ
በእነርሱ ላይ አይደርስም ።
6 ስለዚህ ትዕቢትን እንደ ድሪ
አጥልቀዋል ፤
ዐመፅንም እንደ ልብስ ለብሰዋል ።
7 ልባቸው ክፋትን ያፈልቃል ፤
አእምሮአቸውም በክፉ አሳብ የተሞላ
ነው ።
8 በሌሎች ሰዎች ላይ ይስቃሉ ፤
ክፉ ነገርም ይናገራሉ ፤
ትምክሕተኞች ናቸው ፤
ሌሎችንም ለመጨቈን ያስባሉ ።
9 በሰማይ በሚኖረው አምላክ ላይ
የስድብ ቃል ይናገራሉ ፤
በምድር የሚኖሩትንም ሰዎች
በትዕቢት ያዝዛሉ ።
10 የእግዚአብሔር ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ ወደ
እነርሱ ያዘነብላሉ ፤
የሚነግሩአቸውንም ሁሉ በፍጥነት
ይቀበላሉ ።
11 "እግዚአብሔር ምንም አያውቅም ፤
ልዑል እግዚአብሔር ምንም
አያስተውልም" ይላሉ ።
12 እንግዲህ ክፉዎች እንደዚህ ናቸው ፤
ያላቸው ሀብት በቂ ነው ፤
ዘወትርም ተጨማሪ ሀብት ያገኛሉ ።

13 ታዲያ ኃጢአት ከመሥራት ተቈጥቤ
በንጽሕና የኖርሁት በከንቱ ነውን?
14 አምላክ ሆይ!
ቀኑን ሙሉ እንድሠቃይ አደረግኸኝ ፤
በየማለዳውም ቀጣኸኝ ።

15 ይህን ሁሉ ተናግሬ ብሆን ኖሮ
የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደበደልሁ
በተቈጠርሁ ነበር ።
16 ይህን ችግር ለማስወገድ አሰብሁ ነበር ፤
ነገር ግን ከዐቅሜ በላይ ሆነብኝ ።
17 ወደ መቅደስህ እስክገባ ድረስ
ምንም ለማድረግ አልቻልሁም ፤
ወደ መቅደስህ በገባሁ ጊዜ ግን
በክፉዎች ላይ ምን
እንደሚደርስባቸው ተረዳሁ ።

18 በሚያዳልጥ ስፍራ አኖርሃቸው ፤
ወድቀው እንዲጠፉም አደረግሃቸው ።
19 በቅጽበት ተደመሰሱ ፤
መጨረሻቸውም የሚያስፈራ ሆነ ።
20 እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ስትነሣ
እነርሱ በማለዳ
እንደሚረሳ ሕልም ይጠፋሉ ።

21 አሳቤ መራራ በሆነ ጊዜ ፥
ስሜቴም በተመረዘ ጊዜ ፤
22 እንደ እንስሳ ማስተዋል የጐደለኝ
ሆንሁ ፤
አንተን ማወቅም ተሳነኝ ።
23 ነገር ግን ወደ አንተ ተጠግቼ እኖራለሁ ፤
አንተም ቀኝ እጄን ትይዛለህ ።
24 እየመከርክ ትመራኛለህ ፤
በመጨረሻም በክብር ትቀበለኛለህ ።
25 በሰማይ ከአንተ ሌላ ማን አለኝ?
በምድርስ አንተን ካገኘሁ ፥
ሌላ ምን እሻለሁ?
26 አእምሮዬና ጉልበቱ ሊደክሙ ይችላሉ ፤
እግዚአብሔር ግን እስከ ዘላለም
ብርታቴና እለኝታዬ ነው ።

27 አንተን የሚተው ሁሉ በእርግጥ
ይጠፋሉ ፤
አንተን የሚክዱህን ሁሉ
ትደመስሳቸዋለህ ።
28 ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረቤ
መልካም ነው ፤
የእርሱን ሥራ ሁሉ ለማብሠር
እንድችል
እግዚአብሔር አምላክን መጠጊያዬ
አድርጌአለሁ ።

## ምዕራፍ 74

ስለ ሕዝብ ሰላም የሚቀርብ ጸሎት

1 አምላክ ሆይ!
እንደዚህ ለምን ተውኸን?
ሕዝብህንስ የምትቈጣው ለዘላለም
ነውን?
2 ከጥንት ጀምሮ የመረጥኸውን ፥
የራስህ ወገን እንዲሆን ከባርነት
የዋጀኸውን
ሕዝብህን አስታውስ ፤
ከዚህ በፊት የኖርህበትን
የጽዮንን ተራራ አስብ ።
3 ጠላቶቻችን በመቅደሱ ውስጥ ያለውን
ሁሉ ስላፈራረሱት ፥
ይህን ሊታደስ የማይችለውን ፍርስራሽ
ተዘዋውረህ እይልን ።
4 ጠላቶችህ "ድል አደረግን" ብለው
በቤተ መቅደስህ ውስጥ ይደነፋሉ ፤
በዚያም የድል ምልክት የሆነውን
ሰንደቅ ዓላማ ተክለዋል ።
5 እነርሱ እንጨቶችን በመጥረቢያ
እንደሚቈርጡ
የደን እንጨት ቊራጮችን ይመስላሉ ።
6 በሮችዋን በመጥረቢያና በመዶሻ ሰባበሩ ።
7 መቅደስህን አፍርሰው በእሳት
አቃጠሉት ፤
አንተ የምትመለክበትን ስፍራ
አረከሱት ።
8 ፈጽሞ ሊያጠፉን ፈለጉ ፤
በምድሪቱ ላይ እግዚአብሔር
የሚመለክበትን
ቅዱስ ስፍራ ሁሉ አቃጠሉ ።

9 የተቀደሱ ምልክቶቻችን ሁሉ ጠፉ ፤
ከነቢያትም መካከል የቀረ የለም ፤
ይህ ሁኔታ እስከ መቼ እንደሚቆይ
ከእኛ መካከል የሚያውቅ የለም ።
10 አምላክ ሆይ!
ጠላቶቻችን በአንተ ላይ እየሳቁ
የሚዘባበቱት
እስከ መቼ ነው?
ስምህንስ የሚያጠፉት ለዘላለም
ነውን?
11 እኛን ለመርዳት ያልፈቀድኸው ለምንድን
ነው?
እጅችህንስ ወደ ኋላ አጣምረህ
የምትዘገየው
እስከ መቼ ነው?

12 አምላክ ሆይ!
ከጥንት ጀምሮ ንጉሣችን አንተ ነህ ፤
ብዙ ጊዜም አድነኸናል ።
13 በታላቁ ኀይልህ ባሕሩን ከፈልህ ፤
በባሕር የሚኖሩትን የታላላቅ
አውሬዎች
ራስ ቀጠቀጥህ ፤
14 ሌዋታን የተባለውን የባሕር ዘንዶ ራስ
ቀጠቀጥህ ፤
ሥጋውንም በበረሓ ለሚኖሩ ፍጥረቶች
ምግብ አድርገህ ሰጠሃቸው ።
15 ምንጮችና ጅረቶች ግን እንዲፈስሱ
አደረግህ ፤
ታላላቅ ወንዞችን ግን አደረቅህ ።
16 ቀኑንና ሌሊቱን የፈጠርህ ፥
ፀሐይንና ጨረቃን በየቦታቸው ያጸናህ
አንተ ነህ ፤
17 አንተ ለምድር ዳርቻን ወሰንህ ፤
ክረምትና በጋ እንዲፈራረቁ አደረግህ ።

18 ነገር ግን እግዚአብሔር ሆይ!
ጠላቶችህ በአንተ ላይ እንደሚቀልዱ
ተመልከት ፤
እነርሱ ከሐዲዎች ስለሆኑ አንተን
ይንቃሉ ።

74፥13 ፡- ዘጸ. 14፥21 ። 74፥14 ፡- ኢዮብ 41፥1 ፤ መዝ. 104፥26 ፤ ኢሳ. 27፥1 ።

በእኛም ያለህን ቍጣ አርቅልን ።
5 በእኛ ላይ የምትቈጣው ለዘላለም ነውን?
ለቍጣህስ ገደብ የለውምን?
6 እንደገና እንድንበረታ አድርገን፤
እኛም ሕዝቦችህ እየተደሰትን
እናመሰግንሃለን ።
7 እግዚአብሔር ሆይ!
ዘላለማዊ ፍቅርህን አሳየን፤
እርዳን ፥ አድነንም ።

8 እግዚአብሔር አምላክ የሚነግረኝን ቃል
እሰማለሁ፤
እንደገና በስሕተት መንገድ ካልሄድን
በቀር ፥
ለእኛ ለሕዝቡ ሰላምን እንደሚሰጠን
ቃል ገብቶልናል ።
9 እርሱ የሚፈሩትን ሁሉ ለማዳን ዝግጁ
ነው፤
የማዳኑም ኀይል በምድራችን ላይ
ይኖራል ።
10 ፍቅርና እውነት ይተቃቀፋሉ፤
ጽድቅና ሰላም ይሳሳማሉ ።
11 የሰው ታማኝነት ከምድር ወደ ሰማይ ከፍ
ይላል፤
የእግዚአብሔርም ጽድቅ ከሰማይ ወደ
ምድር ይወርዳል ።
12 እግዚአብሔር ያበለጽገናል፤
ምድራችንም ብዙ የመከር ፍሬ
ትሰጠናለች ።
13 ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ይሄዳል፤
መንገዱንም ያዘጋጅለታል ።

## ምዕራፍ 86

### ከእግዚአብሔር ዕርዳታ ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ!
ደካማና ምስኪን ስለሆንሁ
እባክህ ስማኝ ፥ አድምጠኝም ።
2 በአንተ ታምኛለሁና ከሞት አድነኝ፤
በአንተ ተስፋ ስለማደርግና አንተን
ስለማገለግል ጠብቀኝ ።

3 አንተ አምላኬ ነህና ማረኝ፤
ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጸልያለሁ ።
4 እግዚአብሔር ሆይ!
ጸሎቴ ወደ አንተ ስለሚወጣ ፥
አገልጋይህን ደስ አሰኘው ።
5 አንተ ለእኛ ቸርና መሐሪ ነህ፤
ወደ አንተ ለሚጸልዩትም ሁሉ
ዘላለማዊ ፍቅርህን ታሳያቸዋለህ ።

6 እግዚአብሔር ሆይ! ጸሎቴን ስማ፤
የልመናዬንም ጩኸት አድምጥ ።
7 አንተ ጸሎቴን ስለምትሰማ ፥
በመከራ ጊዜ ወደ አንተ እጮኻለሁ ።

8 ጌታ ሆይ! አንተን የሚመስል አምላክ
የለም፤
አንተ ያደረግኸውን ያደረገ ማንም
የለም ።
9 አንተ የፈጠርኻቸው ሕዝቦች ሁሉ
ወደ አንተ ይመጣሉ፤
ለአንተም ይሰግዳሉ፤
የአንተንም ስም ያከብራሉ ።
10 አንተ ታላቅ ነህ፤ ድንቅ ነገሮችንም
ታደርጋለህ፤
አንተ ብቻ አምላክ ነህ ።

11 እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ የምትፈልገውን ነገር ማድረግን
አስተምረኝ፤
እኔም በታማኝነት እታዘዝሃለሁ፤
በፍጹም ቅንነት እንዳገለግልህ
አስተምረኝ ።
12 ጌታ አምላኬ ሆይ! በሙሉ ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም ለዘላለም አከብራለሁ ።
13 ለእኔ የምታሳየው ዘላለማዊው ፍቅርህ
እንዴት ታላቅ ነው!
ወደ መቃብር ከመውረድ አዳንኸኝ ።
14 አምላክ ሆይ! ትዕቢተኞች በእኔ ላይ
ተነሣሥተዋል፤
አንተን የማይፈሩ ጨካኞች ሰዎች
ሊገድሉኝ
ይፈልጋሉ ።
15 እግዚአብሔር ሆይ!
አንተ ግን መሐሪና ርኅሩኅ አምላክ
ነህ፤
ዘወትር ታጋሽ ፥ ቸርና ታማኝ ነህ ።
16 ፊትህን ወደ እኔ መልስ፤
ምሕረትም አድርግልኝ፤
እናቴ የአንተ አገልጋይ ነበረች፤
እኔም የአንተ አገልጋይ ስለሆንሁ ፥
ብርታትን ስጠኝ ፥ አድነኝም ።
17 እግዚአብሔር ሆይ!
የቸርነትህን ምልክት አሳየኝ፤
አንተ እንደምታጽናናኝና
እንደምትረዳኝ

---

86፥9 ፦ ራእ. 15፥4 ።

በሚያዩበት ጊዜ
ጠላቶቼ ሁሉ ያፍራሉ ።

## ምዕራፍ 87

### ስለ ኢየሩሳሌም የቀረበ ውዳሴ

1 እግዚአብሔር ከተማውን
በተቀደሰው ተራራ ላይ መሠረተ ።
2 በእስራኤል ካሉ ከሌሎች ስፍራዎች
ይልቅ
የኢየሩሳሌምን ከተማ ይወዳል ።
3 አንቺ የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ!
እነሆ እግዚአብሔር ስለ አንቺ
የሚናገረውን
አስደናቂ ነገር ሁሉ አድምጪ ፤

4 "ለእኔ በመታዘዝ የሚያገለግሉኝን
መንግሥታት በምመዘግብበት ጊዜ ፥
ግብጽንና ባቢሎንን እጨምራለሁ ፤
ከኢየሩሳሌም ተወላጆች ጋር
የፍልስጥኤምን ፥ የጢሮስንና
የኢትዮጵያን
ሕዝቦች እጨምራለሁ ።"

5 መንግሥታት ሁሉ በኢየሩሳሌም
ስለተወለዱ ፥
ሁሉም ጽዮንን "እናታችን" ብለው
ይጠሩአታል ።
ልዑል አምላክም ታላቅ ያደርጋታል ።
6 እግዚአብሔር ሕዝቦችን ሁሉ
ይመዘግባል ፤
እያንዳንዱንም "በጽዮን የተወለደ"
ብሎ ይጠራዋል ።
7 እነርሱም "የበረከታችን ሁሉ መገኛ
ጽዮን ናት"
እያሉ በደስታ ይዘምራሉ ።

## ምዕራፍ 88

### የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለማግኘት የቀረበ ልመና

1 አዳኜ የሆንህ እግዚአብሔር አምላክ
ሆይ!
ቀኑን ሙሉ ወደ አንተ እጮኻለሁ ፤
ሌሊቱንም ሙሉ በአንተ ፊት
አለቅሳለሁ ።
2 እባክህ ጸሎቴን ስማ ፤
ጩኸቴንም አድምጥ ።

3 ብዙ መከራ ስለደረሰብኝ ፥
ለመሞት ተቃርቤአለሁ ።
4 ለመሞት እንደተቃረቡት ሰዎች
ሆኜአለሁ ፤
ኀይሌም ሁሉ አልቆአል ።5*
5 ተረስቼ በሙታን መካከል ወድቄአለሁ ፤
አንተ ፈጽሞ የረሳሃቸውንና
የማትረዳቸውን
ሞተው በመቃብር የተኙትን
መስዬአለሁ ።
6 አንተ ወደ መቃብር አዘቅት ጣልኸኝ ፤
ወደ ጨለመውና ጥልቅ ወደሆነው
ጒድጓድ አወረድኸኝ ።
7 ቊጣህ እጅግ ከብዶኛል ፤
የቊጣህም ማዕበል አጥለቅልቆኛል ።

8 ወዳጆቼ ሁሉ ከእኔ እንዲርቁ አደረግህ ፤
በፊታቸውም አስጸያፊ አደረግኸኝ ፤
ተሪያዬ ታጥሮአል ፤ ማምለጫም
የለኝም ።
9 ሐዘኔ ከመብዛቱ የተነሣ ዐይኖቼ ደከሙ ፤
እግዚአብሔር ሆይ! በየቀኑ ወደ አንተ
እጮኻለሁ ፤
እጆቼንም ለጸሎት ወደ አንተ
እዘረጋለሁ ።

10 ለሙታን ተአምራትን ታደርጋለህን?
እነርሱስ ተነሥተው ያመሰግኑሃልን?
11 ዘላለማዊ ፍቅርህ በመቃብር ፥
ታማኝነትህ በጥፋት ቦታ ይነገራልን?
12 ተአምራትህ በዚያ በጨለማ ስፍራ ፥
ታዳጊነትህስ በተረሱ ሰዎች አገር
ይታያልን?

13 እግዚአብሔር ሆይ!
እንድትረዳኝ ወደ አንተ እጮኻለሁ ፤
በየማለዳውም ወደ አንተ እጸልያለሁ ።
14 እግዚአብሔር ሆይ! ለምን ትጥለኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ?
15 ከልጅነቴ ጀምሮ መከራ ደርሶብኛል ፤
ብዙ ጊዜም ለመሞት ተቃርቤአለሁ ፤
ከቅጣትህ ብዛት የተነሣ
ተኰስቊዬአለሁ ።
16 ብርቱ ቊጣህ አደቀቀኝ ፤
አስፈሪ የሆነው ተግሣጽህ አጠፋኝ ።
17 እነርሱ ቀኑን ሙሉ እንደ ጐርፍ
ደረሱብኝ ፤
ዙሪያዬንም ከበቡኝ ።
18 የቅርብ ወዳጆቼንና ጓደኞቼን እንኳ
ከእኔ እንዲርቁና እንዲጸየፉኝ
አደረግህ ፤
ጨለማ ብቻ ጓደኛዬ ሆነ ።

5* 88፥4 ኀይሌም ሁሉ አልቆአል ፦ ወይም "ረዳትም እንደሌለው ሰው ሆንሁ ።"

ከእርሱ ጋር የገባሁትንም ቃል ኪዳን
አጸናለታለሁ።
29 የመንግሥቱም የትውልድ ሐረግ
እንደ ሰማይ የጸና ይሆናል፤
ዘሩም ለዘላለም ይነግሣል።

30 ነገር ግን የእርሱ ዝርያዎች ሕጌን
ቢጥሱ፥
በትእዛዜም መሠረት ባይኖሩ፤
31 መመሪያዎቼን ባይቀበሉ፥
ትእዛዜንም ባይጠብቁ፤
32 በኃጢአታቸው ምክንያት እቀጣቸዋለሁ፤
በበደላቸውም ምክንያት መከራ
አመጣባቸዋለሁ።
33 ነገር ግን ለዳዊት ያለኝ ፍቅር ከቶ
አይገታም፤
ለእርሱ የሰጠሁትንም የተስፋ ቃል
ከመፈጸም
ወደ ኋላ አልልም።
34 ከእርሱ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን
አላፈርስም፤
ለእርሱ ከሰጠሁትም የተስፋ ቃል
አንዱን እንኳ አላስቀርም።

35 በማያዳግም ሁኔታ አንድ ጊዜ በቅዱስ
ስሜ
ስለማልሁ ለዳዊት ከቶ አልዋሽም።
36 ትውልዱ አይቋረጥም፤
መንግሥቱንም ፀሐይ እስከምትኖርበት
ዘመን እጠብቃለሁ።
37 በሰማይ በእውነተኛነት
እንደምትመሰከረው
እንደ ጨረቃም የጸና ይሆናል።”

በንጉሥ ዳዊት መሸነፍ ምክንያት የደረሰ ሐዘን

38 አሁን ግን በመረጥኸው ንጉሥ ላይ
ተቈጥተሃል፤
ተለይተኸዋል፤ ጥለኸዋልም።
39 ከአገልጋይህ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን
አፍርሰሃል፤
ዘውዱንም በዐፈር ላይ ጥለሃል።
40 የከተማውንም ቅጽሮች አፈራርሰሃል፤
ምሽጎቹንም ደምስሰሃል።
41 የመንገድ ተላላፊዎች ሁሉ ንብረቱን
ይዘርፋሉ፤
ጐረቤቶቹ ሁሉ በእርሱ ይስቃሉ።
42 ድልን ለጠላቶቹ ሰጥተህ፥ እንዲደሰቱ
አደረግሃቸው።
43 የጦር መሣሪያዎቹ ከጥቅም ውጪ
እንዲሆኑ አድርገሃል፤
በጦርነትም እንዲሸነፍ
ተለይተኸዋል።
44 በትረ መንግሥቱን ነጠቅኸው፤
ዙፋኑንም በመሬት ላይ ጣልኸበት።
45 ያለ ዕድሜው አስረጀኸው፤
በሐፍረትም ሸፈንከው።

ደኅንነት ለማግኘት የቀረበ ጸሎት

46 እግዚአብሔር ሆይ!
የምትሰወረው ለዘላለም ነውን?
ቊጣህስ እንደ እሳት የሚነደው እስከ
መቼ ነው?
47 ዕድሜዬ ምን ያህል አጭር እንደሆነ
አስብ፤
ሁላችንንም ሟቾች አድርገህ
እንደፈጠርከን አስታውስ።
48 ሰው ሞት ሳይደርስበት እንዲሁ ለመኖር
እንዴት ይችላል?
ወደ መቃብር ሳይወርድ ሊቀርስ
እንዴት ይችላል?

49 እግዚአብሔር ሆይ!
የቀድሞዎቹ የፍቅርህ ማረጋገጫዎች
የት አሉ?
ለዳዊት የሰጠኸውስ የተስፋ ቃል የት
ነው?
50 እኔ አገልጋይህ የቱን ያህል እንደምሰደብ
አስብ፤
የአረማውያንንም ስድብ ተሸክሜ
እንደምኖር አትዘንጋ።
51 እግዚአብሔር ሆይ!
ጠላቶችህ የመረጥኸውን ንጉሥ
ይሰድባሉ፤
በሄደበት ሁሉ ያፌዙበታል።

52 እግዚአብሔርን ለዘላለም አመስግኑ!

አሜን! አሜን!

## ክፍል አራት
(ከመዝሙር 90-106)

## ምዕራፍ 90
### እግዚአብሔርና ሰው

1 እግዚአብሔር ሆይ!
ከዘመናት እስከ ዘመናት መጠጊያ
ሆነኸናል፤
2 ተራራዎችን ከመሥራትህና ዓለምንም
ከመፍጠርህ በፊት፥
ለዘላለም አምላክ ነህ፤
ከእንግዲህ ወዲህም የዘላለም አምላክ
ሆነህ ትኖራለህ።

3 ሰው ወደነበረበት እንዲመለስ
ተናግረሃል፤

ለትዕቢተኞች የሚገባቸውን ቅጣት
ስጣቸው ።
3 ክፉዎች የሚታበዩት እስከ መቼ ነው?
እግዚአብሔር ሆይ! ኧረ እስከ መቼ
ነው?
4 ዐመፀኞች የሚመኩትና ፥
በዐመፅ ሥራቸው የሚታበዩት እስከ
መቼ ነው?

5 እግዚአብሔር ሆይ!
በሕዝብህ ላይ ግፍ ይሠራሉ ፤
የአንተን ወገኖች ይጨቁናሉ ።
6 ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶችና
አባትና እናት የሌላቸውን ልጆች
ይገድላሉ ፤
በምድራችን የሚኖሩትንም መጻተኞች
ያጠፋሉ ።
7 ይህንንም ሁሉ እያደረጉ ፥
"እግዚአብሔር አያየንም ፤
የእስራኤል አምላክ አይመለከተንም"
ይላሉ ።

8 ሕዝቤ ሆይ! እስከዚህ ስንፎችና ሞኞች
ለምን ትሆናላችሁ?
ዕውቀት የምትገበዩትስ መቼ ነው?
9 ጆሮን የፈጠረ እምላክ አይሰማምን?
ዐይንንስ የፈጠረ አምላክ እያይምን?
10 መንግሥታት ሁሉ በእርሱ ቍጥጥር ሥር
ሲሆኑ ሳለ አይቀጣቸውምን?
የሰዎች ሁሉ አስተማሪ ሲሆን ሳለ ፥
ምንም ዕውቀት የለውም ለማለት
ነውን?
11 እግዚአብሔር አሳባቸውን ያውቃል ፤
የማስተዋል ችሎታቸውንም ከንቱነት
ይረዳል ።

12 እግዚአብሔር ሆይ! አንተ
የምትገሥጸውና
ሕግህንም የምታስተምረው ሰው
እንዴት የታደለ ነው!
13 ክፉዎች የሚወድቁበት ጕድጓድ
እስኪቈፈር ድረስ ፥
እርሱን በመከራ ቀኖች ታሳርፈዋለህ ።
14 እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልም ፤
የእርሱ የሆኑትንም አይተዋቸውም ።
15 ፍትሕ እንደገና የጻኝነት መሠረት
ትሆናለች ፤
ልበ ቅኖችም ሁሉ ይደግፉዋታል ።

16 ዐመፀኞችን ለመቃወም ስለ እኔ የቆመ
ማን ነው?
ከክፉ አድራጊዎችስ ጋር ስለ እኔ
የተከራከረ ማን ነው?
17 እግዚአብሔር ባይረዳኝ ኖሮ ፥
ፈጥኜ ወደ ሙታን ዓለም በወረድሁ
ነበር ።
18 "ለመውደቅ ተቃርቤአለሁ" ብዬ ነበር ፤
እግዚአብሔር ሆይ!
ዘላለማዊ ፍቅርህ ግን ደግፎ አቆመኝ ።
19 አሳብና ጭንቀት በያዘኝ ጊዜ ፤
አንተ ታጽናናኛለህ ፤ ደስም
ታሰኘኛለህ ።

20 አንተ ዐመፅን እንደ ጽድቅ ከሚቈጥሩ
ከነውረኞች ፈራጆች ጋር
አትተባበርም ።
21 እነርሱ በደጋግ ሰዎች ላይ ያሤራሉ ፤
በንጹሓን ሰዎች ላይም የሞት ፍርድ
ይበይናሉ ።
22 ለእኔ ግን እግዚአብሔር መከታዬ ነው ፤
አምላኬ ጠባቂዬ ነው ።
23 እርሱ ስለ ክፋታቸው ይቀጣቸዋል ፤
ስለ ኃጢአታቸውም ይደመስሳቸዋል ፤
እግዚአብሔር አምላካችን
ያጠፋቸዋል ።

## ምዕራፍ 95

### የምስጋና መዝሙር

1 ኑ ፥ እግዚአብሔርን እናመስግን ፤
ለሚጠብቀን አምላካችን በደስታ
እንዘምር ።
2 ወደ ፊቱ ቀርበን እናመስግነው ፤
የምስጋና መዝሙሮችን በደስታ
እንዘምርለት ።
3 ምክንያቱም እግዚአብሔር ኀያል አምላክ
ነው ፤
ከአማልክት ሁሉ በላይ የሆነ ታላቅ
ንጉሥ ነው ።
4 ከጥልቅ ዋሻዎች ጀምሮ እስከ ከፍተኛ
ተራራዎች ድረስ ፥
ምድርን በሙሉ ይገዛል ።
5 እርሱ የፈጠራቸውን ባሕርንና ምድርን
ይቈጣጠራል ።

6 ኑ ፥ በእግሩ ሥር ወድቀን እንስገድለት ፤
ፈጣሪያችን በሆነው በእግዚአብሔር
ፊት እንንበርከክ ።
7 እርሱ አምላካችን ነው ፤
እኛም እርሱ የሚጠብቀን
ሕዝቦቹና
የሚያሰማራን መንጋዎቹ ነን ፤

---

94፥11 ፡- 1ቆሮ. 3፡20 ። 95፥7-8 ፡- ዕብ. 3፡15 ፤ 4፡7 ። 95፥7-11 ፡- ዕብ. 3፡7-11 ።

14 እግዚአብሔር ከምን እንደ ተፈጠርን
ያውቃል ፤
ዐፈር መሆናችንንም ያስታውሳል ።

15 እኛ እኮ ሕይወታችን እንደ ሣር ነው ፤
እንደሚያድግና እንደሚያብብ እንደ
ዱር አበባ ነው ።
16 ምክንያቱም የዱር አበባ ነፋስ
በሚነፍስበት ጊዜ
ወዲያው ይጠፋል ፤
በዚያ ስፍራ እንደነበረ እንኳ
አይታወቅም ።
17 ነገር ግን እግዚአብሔር ለሚያከብሩት
ሁሉ
ፍቅሩን ለዘላለም ያሳያቸዋል ፤
ቸርነቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ
ይተላለፋል ።
18 ይህንንም የሚያደርገው ፤
ቃል ኪዳኑን ቢጠብቁ ፤
ትእዛዙንም በታማኝነት ቢፈጽሙ
ነው ።

19 የእግዚአብሔር ዙፋን በሰማይ ነው ፤
የእርሱም መንግሥት ከሁሉ በላይ
ነው ።
20 የሚናገረውን የምታዳምጡ ፤
ትእዛዛቱንም የምትፈጽሙ ፤
እናንተ ኀያላንና ብርቱዎች መላእክቱ
እግዚአብሔርን አመስግኑ ።
21 አገልጋዮቹ የሆናችሁ ፤ ፈቃዱንም
የምትፈጽሙ ፤
እናንተ የሰማይ ኀያላን ፤
እግዚአብሔርን አመስግኑ !
22 በግዛቱ ሁሉ የምትገኙ ፍጥረቶቹ ፤
እግዚአብሔርን አመስግኑ ፤
ነፍሴ ሆይ ! እግዚአብሔርን አመስግኚ ።

## ምዕራፍ 104
### ለፈጣሪ የቀረበ ምስጋና

1 ነፍሴ ሆይ ! እግዚአብሔርን አመስግኚ !
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ! እንዴት
ታላቅ ነህ !
ግርማንና ክብርን ለብሰሃል ፤
2 ብርሃንንም እንደ ልብስ ተጐናጽፈሃል ፤
ሰማይን እንደ ድንኳን ዘርግተሃል ።
3 በጠፈር ላይ ካለው ውሃ በላይ ቤትህን
ሠርተሃል ፤
ደመና ሠረገላህ ነው ፤
በነፋስ ክንፎችም ትሄዳለህ ።
4 ነፋስ መልእክተኛህ ነው ፤
የእሳት ነበልባልም አገልጋይህ ነው ።

5 ምድርን በመሠረትዋ ላይ አጽንተህ
አቆምሃት ፤
ከቶም አትናወጥም ።
6 ውቅያኖስን እንደ ልብስ አለበስሃት ፤
ውሃውም ተራራዎችን ሸፈነ ።
7 ውሃውን በገሠጽኸው ጊዜ ከፊትህ ሸሸ ፤
የትእዛዝህን ድምፅ በሰማ ጊዜ
በፍጥነት ሮጠ ።
8 አንተ ወዳዘጋጀህለት ስፍራ ፤
ወደ ተራሮች ላይና ወደ ሸለቆዎች
ውስጥ ፈሰሰ ።
9 ዳግመኛ ምድርን እንዳይሸፍንም
የማይጥሰውን ወሰን አበጀህለት ።

10 ምንጮች በሸለቆ ውስጥ እንዲፈስሱ ፤
ወንዞችም በተራራዎች መካከል
እንዲወርዱ አደረግህ ።
11 በዚህ ዐይነት የዱር አውሬዎች
የሚጠጡት ውሃ ያገኛሉ ፤
የሜዳ አህዮችም ጠጥተው ጥማቸውን
ያረካሉ ።
12 በነዚህም ምንጮችና ወንዞች አጠገብ
ባሉት ዛፎች ላይ ፤
ወፎች ጎጆአቸውን ሠርተው
ያዜማሉ ።

13 ከሰማይ ዝናምን በተራራዎች ላይ
ታወርዳለህ ፤
ምድርም በምትሰጣት በረከት
ትሞላለች ።
14 ሣርን ለእንስሳት ታበቅላለህ ፤
አትክልትንም ለሰው ልጆች ጥቅም
እንዲውል ታደርጋለህ ፤
በዚህ ዐይነት ሰው ምግብ የሚሆነውን
ዘርቶ ይሰበስባል ።
15 ስለዚህ ልቡን ደስ የሚያሰኝ የወይን
ጠጅ ፤
ፊቱን የሚያበራ ዘይትና
ብርታት የሚሰጠውን ምግብ
ያዘጋጃል ።

16 እግዚአብሔር የተከላቸው
የሊባኖስ የጥድ ዛፎች በቂ ዝናም
ያገኛሉ ፤
17 በላያቸውም ወፎች ጎጆዎቻቸውን
ይሠራሉ ፤
ሽመላዎችም በጥድ ዛፎች ላይ
መኖሪያቸውን ያበጃሉ ።
18 ዋልያዎች በከፍተኛ ተራሮች ላይ
ይገኛሉ ፤

104፥4 ፦ ዕብ. 1፥7 ።

20 የእግዚአብሔርንም ክብር
ሣር በሚበላ እንስሳ ምስል ለወጡ ።
21 በግብጽ ሳሉ ታላላቅ ተአምራት
በማድረግ
ያዳናቸውን አምላክ ረሱ ።
22 በዚያ ሳሉ ያደረገላቸውን አስደናቂ
ነገሮች ዘነጉ ።
በቀይ ባሕርም ያደረገላቸውን
አስገራሚ ነገሮች ዘነጉ ።
23 ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ሕዝቦቹን
ለማጥፋት ዐቅዶ ነበር ፤
ነገር ግን እግዚአብሔር የመረጠው ሙሴ
በመካከል በመቆም ፥
እንዳያጠፋቸውና ቍጣውንም
እንዲመልስ
እግዚአብሔርን ለመነ ።

24 በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
ስላልተማመኑ ፥
መልካሚቱን ምድር ናቁ ።
25 በድንኳኖቻቸው ውስጥ ሆነው
አጕረመረሙ ፤
የእግዚአብሔርንም ቃል አንሰማም
አሉ ።
26 ስለዚህ እጁን አንሥቶ በመማል ፥
በበረሓ የሚያጠፋቸው መሆኑን
ነገራቸው ፤
27 ዝርያዎቻቸውንም ሁሉ በአረማውያን
መካከል
እንደሚበታትናቸውና በመላው ዓለም
ስደተኞች
እንደሚያደርጋቸው ነለጠላቸው ።

28 ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ሕዝብ
በፐዖር የነበረውን ባዓል ተብሎ
የሚጠራውን ጣዖት አመለኩ ፤
ሕይወት ለሌላቸው አማልክት
የቀረበውንም የመሥዋዕት ሥጋ በሉ ።
29 በክፉ ሥራቸው እግዚአብሔርን
አስቈጡት ፤
በዚህ ምክንያት ቀሣፊ በሽታ
በመካከላቸው ተነሣ ።
30 ነገር ግን ፊንሐስ ተነሥቶ ፥
በደል የፈጸሙትን በቀጣቸው ጊዜ ፥
ቀሣፊው በሽታ ተወገደ ።
31 ይህም አድራጎቱ መልካም ሥራ ሆኖ
ተቈጠረለት ፤
ወደ ፊትም ለዘመናት ሁሉ የእርሱ
መታሰቢያ
ሆኖ ይኖራል ።

32 በመሪባ ምንጮች አጠገብ
ሕዝቡ እግዚአብሔርን አስቈጡት ፤
በእነርሱም ምክንያት ሙሴ ችግር ላይ
ወደቀ ።
33 እጅግ አስመርረውት ስለነበር
ሙሴ ራሱን ባለመቈጣጠር ተናገረ ።

34 እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት ፥
አረማውያንን አላጠፉም ፤
35 እንዲያውም ከእነርሱ ጋር ተደባልቀው ፥
የኑሮ ሥርዓታቸውን ተከተሉ ።
36 የእግዚአብሔር ሕዝቦች
የአረማውያንን ጣዖታት አመለኩ ፤
ይህም ለጥፋታቸው ምክንያት ሆነ ።
37 ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን
በከነዓን አገር ለሚገኙ ጣዖታት
መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ ።
38 እነዚያን ምንም የማያውቁትን የዋሆች
ሕፃናት ገደሉ ፤
ምድሪቱም በግፍ ግድያ ረከሰች ።
39 እነርሱ በሥራቸው ረከሱ ፤
ክፉ ምኞታቸውንም ተከትለው
እግዚአብሔርን ካዱ ።

40 ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተቈጣ ፤
እጅግም ተጸየፋቸው ።
41 ለአረማውያን አሳልፎ ሰጣቸው ፤
ጠላቶቻቸውም ገዦዎቻቸው ሆኑ ።
42 በጠላቶቻቸው ተጨቍነው ፥
ፈጽሞ የእነርሱ ተገዦዎች ሆኑ ፤
43 እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ሕዝቡን
ታድጎአቸዋል ፤
እነርሱ ግን በእርሱ ላይ ማመፅን
መረጡ ፤
ስለዚህ ኃጢአታቸው ይበልጥ እየበዛ
ሄደ ።
44 ይህም ሁሉ ሆኖ ፥
እንደገና ወደ እግዚአብሔር
በሚጮኹበት ጊዜ
ይሰማቸው ነበር ፤
ሥቃያቸውንም ይመለከት ነበር ።
45 እነርሱን ለማዳን ቃል ኪዳኑን ያስታውስ
ነበር ፤
ስለ ታላቅ ፍቅሩም ምሕረት
ያደርግላቸው ነበር ።
46 የሚጨቍኑአቸው ሁሉ
እንዲራሩላቸው አደረገ ።

47 እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ!
እባክህ አድነን ፤

106፥24-26 ፦ ዘኍ. 14፥1-35 ። 106፥27 ፦ ዘሌ. 26፥33 ። 106፥28-31 ፦ ዘኍ. 25፥1-13 ።
106፥32-33 ፦ ዘኍ. 20፥2-13 ። 106፥34-36 ፦ መሳ. 2፥1-3 ፤ 3፥5-6 ። 106፥37 ፦ 2ነገ. 17፥17 ።
106፥38 ፦ ዘኍ. 35፥33 ። 106፥40-46 ፦ መሳ. 2፥14-18 ። 106፥47-48 ፦ 1ዜ.መ. 16፥35-36 ።

ከመንግሥታትም መካከል መልሰህ
ወደ አገራችን አግባን ፤
በዚያን ጊዜ እናመሰግንሃለን ፤
ቅዱስ ስምህንም እናከብራለን ።

48 የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
የተመሰገነ ይሁን ፤
አሁንም ዘላለምም አመስግኑት ፤
ሰው ሁሉ አሜን ይበል ።

እግዚአብሔር ይመስገን!

## ክፍል አምስት
(ከመዝሙር 107-150)

## ምዕራፍ 107
### ስለ እግዚአብሔር ቸርነት የሚቀርብ ምስጋና

1 ቸር ስለሆነና ፍቅሩም ዘላለማዊ ስለሆነ
እግዚአብሔርን አመስግኑ ።
2 እናንተ እግዚአብሔር ያዳናችሁ ሁሉ
ዘወትር አመስግኑት ፤
እርሱ ከጠላቶቻችሁ እጅ
ታድጎአችኋል ።
3 ከባዕድም አገር መልሶ አምጥቶአችኋል ፤
ከምሥራቅና ከምዕራብ ፥
ከሰሜንና ከደቡብ[6*] ሰብስቦአችኋል ።

4 አንዳንዶች የመንገዳቸውን አቅጣጫ
በመሳት
በበረሓ ተንከራተቱ ፤
ወደሚኖሩበት ከተማ የሚመራቸውን
መንገድ
ለማግኘት አልቻሉም ።
5 ተርበውና ተጠምተው ስለነበር ፥
ተስፋ ቈረጡ ።
6 በመከራቸውም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ ፤
እርሱም ከጭንቀታቸው አዳናቸው ።
7 ወደሚኖሩባትም ከተማ
በትክክለኛ መንገድ መራቸው ።
8 ስላደረገላቸው ድንቅ ነገሮችና ስለ
ዘላለማዊ ፍቅሩ
እግዚአብሔርን ያመስግኑ ።
9 እርሱ የተጠሙትን ያረካቸዋል ፤
የተራቡትንም ብዙ መልካም ነገር
በመስጠት ያጠግባቸዋል ።

10 ከእነርሱም መካከል አንዳንዶቹ ጥቅጥቅ
ባለ
ጨለማ ውስጥ ይኖሩ ነበር ፤
በሰንሰለትም ታስረው ይሠቃዩ ነበር ።
11 ይህም ሁሉ የደረሰባቸው በልዑል
እግዚአብሔር
ትእዛዝ ላይ በማመፃቸውና
ምክሩንም ባለመቀበላቸው ነበር ።
12 ከሥራ ብዛት የተነሣ ደከሙ ፤
በወደቁም ጊዜ የሚረዳቸው
አላገኙም ።
13 በመከራቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ ፤
እርሱም ከጭንቀታቸው አዳናቸው ።
14 ከወደቀባቸው ድቅድቅ ጨለማ
አወጣቸው ፤
የታሰሩበትንም እግር ብረት ሰባበረ ።
15 ስላደረገላቸው ድንቅ ነገሮችና
ስለ ዘላለማዊ ፍቅሩ እግዚአብሔርን
ያመስግኑ ።
16 ከናስ የተሠሩትን በሮች ሰባበረ ፤
የብረት መወርወሪያዎችንም ቈራረጠ ።

17 አንዳንዶቹም ከኃጢአታቸውና
ከበደላቸው ብዛት
የተነሣ ሥቃይ ደረሰባቸው ፤
እንደ ሞኞችም ተቈጠሩ ።
18 ምግብ በዐይናቸው እንኳ ለማየት ስለጠሉ
ለመሞት ተቃርበው ነበር ።
19 ከዚህ በኋላ በመከራቸው ጊዜ ወደ
እግዚአብሔር ጮኹ ፤
እርሱም ከጭንቀታቸው አዳናቸው ።
20 ቃሉን ላከ ፤ ፈወሳቸውም ፤
ከመሞትና ወደ መቃብር ከመውረድ
አዳናቸው ።
21 ስላደረገላቸው ድንቅ ነገሮችና
ስለ ዘላለማዊ ፍቅሩ እግዚአብሔርን
ያመስግኑ ።
22 መሥዋዕት በማቅረብ ያመስግኑት ፤
የምስጋና መዝሙር በመዘመር
ያደረገውን ሁሉ ይናገሩ ።

23 አንዳንዶች በመርከብ ተሣፍረው በባሕር
ላይ ይጓዙ ነበር ፤
በታላላቅ ውሃዎችም ላይ እየሠሩ
ይተዳደሩ ነበር ።
24 እነርሱ የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ አዩ ፤
በጥልቅ ባሕርም ውስጥ
የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ
ተመለከቱ ።
25 ትእዛዝ በሰጠ ጊዜ ዐውሎ ነፋስ ነፈሰ ፤
ማዕበሉም ተንቀሳቀሰ ።

---

6* 107፥3 ከደቡብ ፦ ወይም "ከሜድትራኒያን ባሕር ።"

107፥1 ፦ 1ዜ.መ. 16፥34 ፤ 2ዜ.መ. 5፥13 ፤ 7፥3 ፤ ዕዝ. 3፥11 ፤ መዝ. 100፥5 ፤ 106፥1 ፤ 118፥1 ፤ 136፥1 ፤ ኤር. 33፥11 ።

እስከ ኤዶምስ ማን ይመራኛል?
11 አምላክ ሆይ! አንተ ጥለኸናል፤
ከሠራዊታችንም ጋር ወደ ጦር ሜዳ
መውጣት ትተሃል።
12 የሰው ዕርዳታ ከንቱ ነው፤
ስለዚህ ጠላቶቻችንን ድል
እንድናደርግ አንተው እርዳን።
13 እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ
እናሸንፋለን!
እርሱ ጠላቶቻችንን ያዋርዳቸዋል።

## ምዕራፍ 109

በመከራ ላይ የሆነ ሰው ጸሎ

1 አምላክ ሆይ! አመሰግንሃለሁ፤
ምስጋናዬንም ቸል አትበልብኝ።
2 ክፉዎችና ሐሰተኞች ተቃውመውኛል፤
በእኔ ላይ በሐሰት ይናገራሉ።
3 ያለ ምክንያት ያስጨንቁኛል፤
በእኔ ላይ ክፉ ቃል ይናገራሉ።
4 ምንም እንኳ እኔ የምወዳቸውና
የምጸልይላቸው ብሆንም፥
እነርሱ ይቃወሙኛል።
5 በመልካም ፈንታ ክፉ፥ በፍቅር ፈንታ
ጥላቻ፥
ይመልሱልኛል።

6 በጠላቴ ላይ የሚፈርድ ዐመፀኛ ዳኛ
ሠይም፤
ከጠላቶቼም አንዱ እንዲከሰሰው
አድርግ፤
በተሟገተ ጊዜ ተረትቶ ይመለስ፤
7 ጸሎቱ እንኳ እንደ ኃጢአት
ይቈጠርበት፤
8 ዕድሜውም በቶሎ ይቀጭ፤
ሥራውንም ሌላ ሰው ይውሰድበት።
9 ልጆቹ ያለ አባት ይቅሩ፤
ሚስቱም ባል የሌላት ትሁን።
10 ልጆቹ ቤት የሌላቸው ለማኞች ይሁኑ፤
አሁን ከሚኖሩበት ወና ቤት እንኳ
ይባረሩ።
11 ንብረቱ ሁሉ በዕዳ ይያዝበት፤
ለፍቶ ያገኘውን ጥሪት ሁሉ
ባዕዳን ሰዎች ይውሰዱበት።
12 የሚራራለት ሰው ከቶ አይኑር፤
ድኻ አደግ ልጆቹን የሚከባከባቸው
ሰው አይገኝ።
13 ለሰሙ መጥሪያ የሚሆን አንድ ልጅ
እንኳ አይቅርለት፤
ከአንድ ትውልድ በኋላ
የሚያስታውሰው አይኑር።
14 እግዚአብሔር የቀድሞ አባቶቹን ኃጢአት
ያስብበት፤
የእናቱንም ኃጢአት ይቅር
አይበልላት።
15 እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ዘወትር
ያስታውስ፤
እነርሱ ራሳቸው ግን ፈጽሞ የተረሱ
ይሁኑ።

16 ሰውየው ደግ ሥራ ለማድረግ ፈጽሞ
አላሰበም፤
ድኾችን፥ ችግረኞችንና ምስኪኖችን
እያሳደደ
ይገድል ነበር።
17 መራገም ይወድድ ስለነበር፥ እርሱም
የተረገመ ይሁን፤
መመረቅን ይጠላ ስለነበር፤ እርሱንም
የሚመርቅ
ሰው አይኑር።
18 መራገም ልብስ የመልበስ ያህል
ይቀልለው ነበር፤
ስለዚህ የራሱ እርግማን እንደ ውሃ
ወደ ሰውነቱ ገብቶ ያረስርሰው፤
እንደ ዘይትም ወደ አጥንቱ ዘልቆ
ይግባ።
19 እንደ ልብስ ይሸፍነው፤
እንደ ቀበቶም ዘወትር በወገቡ ዙሪያ
ይሁን።

20 እግዚአብሔር ሆይ!
ይህን ሁሉ ክፉ ነገር በእኔ ላይ
የሚናገሩትን
ጠላቶቼን በዚህ ዐይነት ቅጣቸው።
21 እግዚአብሔር አምላኪ ሆይ!
እኔን ግን በገባህልኝ ቃል ኪዳን
መሠረት እርዳኝ፤
በመልካም ቸርነትህም ታደገኝ።
22 እኔ ድኻና ምስኪን ነኝ፤
የደረሰብኝም መከራ ልቤን
አስጨንቆታል።
23 እንደ ማታ ጥላ ላልፍ ተቃርቤአለሁ፤
እንደ አንበጣም በነፋስ
ተወስጄአለሁ።
24 ጒልበቶቼ በጾም ደከሙ፤
ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ።
25 ሰዎች እኔን በማየት ይሰቃሉ፤
በንቀትም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።

26 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! እባክህ
እርዳኝ፤
ስለ ዘላለማዊው ፍቅርህም አድነኝ!

---

109፥8 ፦ ሐ.ሥ. 1፥20። 109፥25 ፦ ማቴ. 27፥39፤ ማር. 15፥29።

27 የምታድነኝ አንተ ብቻ እንደሆንህ
ጠላቶቼ እንዲያውቁ አድርግ ።
28 እነርሱ ይረግሙኛል ፤
አንተ ግን ትመርቀኛለህ ፤
አሳዳጆቼን አዋርዳቸው ፤
እኔን አገልጋይህን ግን ደስ አሰኘኝ ።
29 ጠላቶቼ ውርደትን እንደ ልብስ ይልበሱ ፤
ሐፍረትንም እንደ መጐናጸፊያ
ይደርቡ ።

30 ድምፄን ከፍ አድርጌ እግዚአብሔርን
አመሰግናለሁ ፤
በሕዝብ ጉባኤ መካከል አከብረዋለሁ ።
31 ምክንያቱም እርሱ ስለ ድኻ ሰው መብት
ይከራከራል ፤
ሊገድሉት ከተዘጋጁ ሰዎችም እጅ
ያድነዋል ።

## ምዕራፍ 110

### እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ

1 እግዚአብሔር ለጌታዬ (ለመሲሑ)
"ጠላቶችህን በሥልጣንህ ሥር
እስከማደርግልህ ድረስ በቀኜ
ተቀመጥ" አለው ።
2 እግዚአብሔር የኀይልን ብትር ሰጥቶ
የመንግሥትህን ሥልጣን ከጽዮን
ያስፋልህ ፤
በጠላቶችህ ላይ ሥልጣን ይኑርህ ።
3 በተወለድህ ጊዜ ቅድስናህ ያንጸባርቅ
ነበር ፤
ከማኅፀን ከወጣህበት ጊዜ ጀምሮ ፥
እንደ ጠዋት ጠል ነበርህ ።

4 እግዚአብሔር "በመልከ ጼዴቅ ሹመት
ለዘላለም
ካህን ትሆናለህ" ብሎ ማለ ፥
መሐላውም የማይሻር ነው ።

5 እግዚአብሔር በቀኝህ ነው ፤
በሚቈጣበት ጊዜ ነገሥታትን
ድል ነሥቶ ይሰባብራቸዋል ።
6 በመንግሥታት ላይ ይፈርዳል ፤
የጦር ሜዳዎችንም ሬሳ በሬሳ
ያደርጋል ፤
በምድር ላይ ያሉትን ነገሥታት ሁሉ
ይደመስሳል ።
7 ንጉሡ ከመንገድ ዳር ካለው ምንጭ
ከጠጣ በኋላ
ኀይሉን በማደስ በድል አድራጊነት
ጸንቶ ይቆማል ።

## ምዕራፍ 111

### ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና

1 እግዚአብሔር ይመስገን ፤
በቅኖች ሸንጎና በጉባኤም መካከል
እግዚአብሔርን በሙሉ ልቤ
አመሰግናለሁ ።
2 የእግዚአብሔር ሥራዎች አስደናቂዎች
ናቸው ።
በእነርሱ የሚደሰቱ ሰዎች ሁሉ
እነርሱን ለማወቅ
ይፈልጋሉ ።
3 የእግዚአብሔር ሥራ በክብርና በግርማ
የተሞላ ነው ፤
ጽድቁም ዘላለማዊ ነው ።

4 እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ስለሆነ
አስደናቂ
ሥራው ዘወትር እንዲታወስ አደረገ ፤
5 ለሚፈሩት ሁሉ ምግባቸውን
ያዘጋጅላቸዋል ፤
ቃል ኪዳኑንም ከቶ አይረሳም ።
6 የባዕዳንን ርስት በመስጠት
ታላቅ ኀይሉን ለወገኖቹ አሳይቶአል ።

7 የሚያደርገው ሁሉ እውነትና ትክክል
ነው ፤
ትእዛዛቱም የታመኑ ናቸው ፤
8 ለዘላለምም የጸኑ ናቸው ፤
የተሰጡትም በእውነትና በቅንነት
አሳብ ነው ።
9 ሕዝቡን ነጻ አወጣቸው ፤
ከእነርሱም ጋር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን
ገባ ፤
እርሱ ቅዱስና ኀያል ነው ።
10 እግዚአብሔርን መፍራት
የጥበብ መጀመሪያ ነው ፤
ትእዛዙን የሚፈጽሙትን ሁሉ
አስተዋዮች ያደርጋቸዋል ።
እግዚአብሔር ለዘላለም የተመሰገነ
ይሁን ።

## ምዕራፍ 112

### የደግ ሰው ደስታ

1 እግዚአብሔር ይመስገን ፤
እግዚአብሔርን የሚፈራና

110፥1 ፦ ማቴ. 22፥44 ፤ ማር. 12፥36 ፤ ሉቃ. 20፥42-43 ፤ ሐ.ሥ. 2፥34-35 ፤ 1ቆሮ. 15፥25 ፤ ኤፌ. 1፥20-22 ፤ ቆላ. 3፥1 ፤ ዕብ. 1፥13 ፤ 8፥1 ፤ 10፥12-13 ። 110፥4 ፦ ዕብ. 5፥6 ፤ 6፥20 ፤ 7፥17 ፣21 ። 111፥10 ፦ ኢዮብ 28፥28 ፤ ምሳ. 1፥7 ፤ 9፥10 ።

## ምዕራፍ 115
### እውነተኛ የሆነ አንድ አምላክ

[1] እግዚአብሔር አምላክ ሆይ!
ስለ እኛ ሳይሆን ፥
ስለ ዘላለማዊው ፍቅርህና ስለ
እውነተኛነትህ
ስምህን አክብረው ።

[2] አረማውያን
"አምላካችሁ የት አለ?" እያሉ
ስለምን ይዘባበቱብናል?
[3] አምላካችን በሰማይ ነው ፤
እርሱ ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ
ያደርጋል ።
[4] እነርሱ የሚያመልኩአቸው ጣዖቶች ግን
በሰው እጅ
ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ናቸው ።
[5] አፍ አላቸው ፥ አይናገሩም ፤
ዐይን አላቸው ፥ አያዩም ፤
[6] ጆሮ አላቸው ፥ አይሰሙም ፤
አፍንጫ አላቸው ፥ አያሸቱም ፤
[7] እጅ አላቸው ፥ አይዳስሱም ፤
እግር አላቸው ፥ አይሄዱም ፤
ድምፅም ማሰማት አይችሉም ።
[8] የሠሩአቸውና የሚታመኑባቸው ሁሉ
እንደነዚህ ጣዖቶች ይሁኑ ።

[9] እናንተ የእስራኤል ሕዝብ ግን ፥
የሚረዳችሁና የሚጠብቃችሁ
እግዚአብሔር ስለሆነ
በእርሱ ታመኑ ።
[10] እናንተ የእግዚአብሔር ካህናት ፥
የሚረዳችሁና የሚጠብቃችሁ እርሱ
ስለሆነ
በእግዚአብሔር ታመኑ ።
[11] እናንተ የምትፈሩት ሁሉ
የሚረዳችሁና የሚጠብቃችሁ እርሱ
ስለሆነ
በእግዚአብሔር ታመኑ ።

[12] እግዚአብሔር ያስታውሰናል ፤ ደግሞም
ይባርከናል ፤
የእስራኤልን ሕዝብና የእግዚአብሔርን
ካህናት
ሁሉ ይባርካል ።
[13] የሚፈሩትን ሁሉ ፥
ታላላቆችንም ሆነ ታናናሾችን
ይባርካል ።

[14] እግዚአብሔር እናንተና ልጆቻችሁ
እንድትበዙ ያድርጋችሁ ።
[15] ሰማይንና ምድርን የፈጠረ
እግዚአብሔር ይባርካችሁ ።
[16] ሰማይ የእግዚአብሔር ነው ፤
ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጥቶአል ።
[17] ወደ ዝምታ ዓለም ፥ ወደ መቃብር
የወረዱ ሙታን
እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑት
አይችሉም ።
[18] እኛ ግን በሕይወት ያለነው ፥
ከአሁኑ ጊዜ ጀምሮ ዘላለም
እናመሰግነዋለን ።

እግዚአብሔር ይመስገን!

## ምዕራፍ 116
### ከሞት የዳነ ሰው ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና

[1] ጩኸቴንና ልመናዬን ስለ ሰማ
እግዚአብሔርን እወደዋለሁ ።
[2] እርሱን በምጠራው ጊዜ ሁሉ
ይሰማኛል ።
[3] የሞት አደጋ ዙሪያዬን ከበበኝ ፤
የመቃብር አስፈሪ ሁኔታ አሠቃየኝ ፤
በፍርሃትና በጭንቀትም ተሞላሁ ።
[4] በዚያን ጊዜ "አምላክ ሆይ! እባክህ
አድነኝ!"
ብዬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ ።

[5] እግዚአብሔር መሐሪና ቸር ነው ።
አምላካችን ርኅሩኅ ነው ።
[6] እግዚአብሔር የዋሆች የሆኑትን
ይጠብቃል ፤
እኔንም በተዋረድሁ ጊዜ አድኖኛል ።
[7] እግዚአብሔር መልካም ነገር
ስላደረገልሽ ፥
ነፍሴ ሆይ! ወደ እረፍትሽ ተመለሺ ።

[8] እግዚአብሔር ከሞት አዳነኝ ፤
እንባዬ እንዲቆም አደረገ ፤
ከመዋረድም ጠበቀኝ ።
[9] ስለዚህ ሕያዋን በሚገኙበት
በእግዚአብሔር ፊት እኖራለሁ ።
[10] "እጅግ ተሠቃየሁ!" ባልሁበት ጊዜ
እንኳ ፥
እምነቴን አልተውሁም ።
[11] ከፍርሃቴ የተነሣ "ማንንም ማመን
አልችልም"
ባልሁበት ጊዜ እንኳ ፥
እምነቴን አልተውሁም ።

115፥4-8 ፦ መዝ. 135፥15-18 ፤ ራእ. 9፥20 ። 115፥13 ፦ ራእ. 11፥18 ፤ 19፥5 ። 116፥10 ፦ 2ቆሮ. 4፥13 ።

[12] ስላደረገልኝ መልካም ነገር ሁሉ፥
ለእግዚአብሔር ምን ውለታ ልመልስ
እችላለሁ?
[13] እግዚአብሔር ስላዳነኝ አመሰግነዋለሁ፤
የወይን ጠጅ መባም አቀርብለታለሁ።
[14] በሕዝብ ጉባኤ ፊት ተገኝቼ
ለእግዚአብሔር የተሳልሁትን
አቀርባለሁ።

[15] የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ
እጅግ የከበረና ዋጋ ያለው ነው።
[16] እግዚአብሔር ሆይ! እኔ የአንተ አገልጋይ
ነኝ፤
እናቴ እንዳገለገለችህ፥ እኔም
አገለግልሃለሁ፤
ከሞት ያዳንከኝ አንተ ነህ።
[17] የምስጋና መሥዋዕት አቀርብልሃለሁ፤
ወደ አንተም እጸልያለሁ።
[18] በሕዝብ ጉባኤ ፊት ተገኝቼ፥
ለእግዚአብሔር የተሳልሁትን
አቀርባለሁ፤
[19] የማቀርበውም በኢየሩሳሌም መካከል
በሚገኘው በእግዚአብሔር ቤት
አደባባይ ነው።

እግዚአብሔር ይመስገን!

## ምዕራፍ 117

ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና

[1] መንግሥታት ሁሉ እግዚአብሔርን
አመስግኑት!
ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን
አመስግኑት!
[2] እርሱ ለእኛ ያለው ፍቅር ጽኑ ነው፤
ታማኝነቱም ዘላለማዊ ነው።

እግዚአብሔር ይመስገን!

## ምዕራፍ 118

ስለ ድል አድራጊነት የቀረበ የምስጋና ጸሎት

[1] ቸር ስለሆነና ፍቅሩም ዘላለማዊ ስለሆነ
እግዚአብሔርን አመስግኑ።
[2] የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ
"የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ
ነው" ይበሉ።
[3] የእግዚአብሔር ካህናት ሁሉ
"የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ
ነው" ይበሉ።
[4] የሚያከብሩት ሁሉ
"የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ
ነው" ይበሉ።

[5] በተጨነቅሁ ጊዜ ጩኸቴን ወደ
እግዚአብሔር አሰማሁ፤
እርሱም ሰማኝ፤ ነፃም አወጣኝ።
[6] እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ሆኖ ስለሚረዳኝ
አልፈራም፤
ከቶ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
[7] እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ሆኖ
ስለሚረዳኝ፥
ጠላቶቼ ሲዋረዱ አያለሁ።
[8] በሰው ከመመካት ይልቅ፥
በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።
[9] በመሪዎች ከመመካት ይልቅ፥
በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።

[10] ብዙ ጠላቶች ከብበውኝ ነበር፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል
አሸነፍሁአቸው።
[11] ከየአቅጣጫው በዙሪያዬ ነበሩ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል
አሸነፍሁአቸው።
[12] ዙሪያዬን እንደ ንብ ከበቡኝ፤
ነገር ግን እሾኽ በእሳት እንደሚቃጠል
በፍጥነት ተቃጠሉ፤
በእግዚአብሔርም ኃይል
አሸነፍሁአቸው።
[13] ብርቱ ጥቃት ደርሶብኝ፥
ለመሸነፍ ተቃርቤ ነበር፤
ነገር ግን እግዚአብሔር ረዳኝ።
[14] ኃይልንና ብርታትን የሰጠኝ
እግዚአብሔር ነው፤
ያዳነኝም እርሱ ነው።

[15] በእግዚአብሔር ሕዝብ ድንኳን ውስጥ
እንዲህ የሚል የድል አድራጊነት
ድምፅ ይሰማል፥
"የእግዚአብሔር ብርቱ ኃይል ይህን
አድርጎአል!
[16] የእርሱ ኃይል ድልን አጐናጸፈን፤
የቀኝ እጁ ብርታት ታላላቅ ነገሮችን
አደረገልን።"

[17] በሕይወት እኖራለሁ እንጂ አልሞትም፤
የእግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ
ዐውጃለሁ።
[18] በብርቱ ቀጥቶኛል፤
ነገር ግን እንድሞት አላደረገኝም።

---

117፥1 ፦ ሮም 15፥11። 118፥1 ፦ 1ዜ.መ. 16፥34፤ 2ዜ.መ. 5፥13፤ 7፥3፤ ዕዝ. 3፥11፤ መዝ. 100፥5፤ 106፥1፤ 107፥1፤ 136፥1፤ ኤር. 33፥11። 118፥6 ፦ ዕብ. 13፥6። 118፥14 ፦ ዘጸ. 15፥2፤ ኢሳ. 12፥2።

19 ወደ ውስጥ ገብቼ እግዚአብሔርን
እንዳመሰግን
የቤተ መቅደስን በሮች ክፈቱልኝ ።

20 ይህ የእግዚአብሔር በር ነው ፤
በእርሱ ሊገቡ የሚችሉ ደጋግ ሰዎች
ብቻ ናቸው ።

21 እግዚአብሔር ሆይ !
ስለ ሰማኸኝና ድልን ስላጐናጸፍኸኝ
አመሰግንሃለሁ ።

22 ግንበኞች የናቁት ድንጋይ
እርሱ ዋና የማእዘን ድንጋይ ሆነ ፤
23 ይህም የእግዚአብሔር ሥራ ነው ፤
ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው ።
24 ይህ እግዚአብሔር የሠራው የድል ቀን
ነው ፤
በእርሱ ደስ ይበለን ፤ ሐሴትም
እናድርግ ።
25 እግዚአብሔር ሆይ ! እባክህ አድነን ፤
እግዚአብሔር ሆይ ! እባክህ ሁሉ ነገር
የተሟላ እንዲሆን አድርግልን ።

26 በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ
ይሁን ፤
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆነን
እንባርካችኋለን ።
27 እግዚአብሔር አምላክ ነው ፤
ለእኛ መልካም አድርጎልናል ፤
ለምለም የሆኑ ቅርንጫፎች ይዛችሁ
በዓል አድርጉ ፤
መሠዊያውንም ዙሩ ።
28 አንተ አምላኬ ስለሆንህ አመሰግንሃለሁ ፤
ታላቅነትህንም ዐውጃለሁ ።

29 ቸር ስለሆነና ፍቅሩም ዘላለማዊ ስለሆነ ፥
እግዚአብሔርን አመስግኑት ።

## ምዕራፍ 119

### አሌፍ

### የእግዚአብሔር ሕግ

1 በአካሄዳቸው ቅኖች የሆኑ ፥
በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት የሚኖሩ
ሰዎች
ደስ ይበላቸው ።
2 ትእዛዛቱን የሚጠብቁ ፥
በሙሉ ልባቸውም የሚያገለግሉት ፥
ደስ ይበላቸው ።
3 እንደዚህ የሚያደርጉ ክፉ አይሰሩም ፤
የሚኖሩትም የእግዚአብሔርን ፈቃድ
በመፈጸም ነው ።
4 እግዚአብሔር ሆይ ! አንተ ሕጎችህን
ሰጥተኸናል ፤
በታማኝነት እንድንታዘዛቸውም
ነግረኸናል ፤
5 ሥርዓትህን በመጠበቅ ታማኝ ለመሆን
በብርቱ እመኛለሁ ።
6 ትእዛዛትህን ሁሉ በጥንቃቄ
ከአስተዋልሁ ፥
ሐፍረት ከቶ አይደርስብኝም ።
7 እውነተኛ ፍርድህን ባወቅሁ መጠን ፥
በንጹሕ ልብ አመሰግንሃለሁ ።
8 ሕግህን ስለምፈጽም
ፈጽሞ አትተወኝ ።

### ቤት

### ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ

9 ወጣቶች ሕይወታቸውን በንጽሕና
መጠበቅ የሚችሉት ፥
ትእዛዛትህን በመፈጸም ነው ።
10 አንተን በሙሉ ልቤ ማገልገል
ስለምፈልግ ፥
ትእዛዛትህን እንዳላፈርስ ጠብቀኝ ።
11 አንተን እንዳልበድል ፥
ቃልህን በልቤ አኖራለሁ ።
12 እግዚአብሔር ሆይ ! አመሰግንሃለሁ ፤
የአንተን መንገድ አስተምረኝ ።
13 አንተ የሰጠኸውን ሕግ ሁሉ
መሳልሼ አነባለሁ ።
14 ብዙ ሀብት ከሚኖረኝ ይልቅ ፥
የአንተን ትእዛዝ መፈጸም ደስ
ይለኛል ።
15 ሥርዓትህን አጠናለሁ ፤
ትምህርትህንም አሰላስላለሁ ።
16 በሕግህ ደስ ይለኛል ፤
ቃልህንም አልረሳም ።

### ጋሜል

### ከእግዚአብሔር ሕግ የሚገኝ ደስታ

17 በሕይወት እንድኖርና የቃልህን
ትምህርት እንድጠብቅ ፥
ለእኔ ለአገልጋይህ መልካም ነገር
አድርግልኝ ።
18 በሕግህ ውስጥ ያለውን አስደናቂ እውነት
ማየት እንድችል ፥ ዐይኖቼን
ክፈትልኝ ።
19 እኔ በምድር ላይ በእንግድነት የምኖረው
ለጥቂት ጊዜ ነው ፤

---

118፥22 ፦ ሉቃ. 20፥17 ፤ ሐ.ሥ. 4፥11 ፤ 1ጴጥ. 2፥7 ። 118፥22-23 ፦ ማቴ. 21፥42 ፤ ማር. 12፥10-11 ።
118፥25 ፦ ማቴ. 21፥9 ፤ ማር. 11፥9 ፤ ዮሐ. 12፥13 ። 118፥26 ፦ ማቴ. 21፥9 ፤ 23፥39 ፤ ማር. 11፥9 ፤
ሉቃ. 13፥35 ፤ 19፥38 ፤ ዮሐ. 12፥13 ።

4 እግዚአብሔር ሆይ!
ትእዛዛትህን ለሚፈጽሙ ደጋግ
ሰዎች ፥
ቸርነት አድርግላቸው ።
5 ነገር ግን በመፀኞችን በምትቀጣበት
ጊዜ ፥
የእንተን መንገድ የተዉትን
ከሐዲዎችንም አብረህ ቅጣቸው ።

ሰላም ከእስራኤል ጋር ይሁን!

## ምዕራፍ 126

ከምርኮ በደስታ ስለመመለስ የቀረበ ምስጋና

1 እግዚአብሔር ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ
ባመጣን ጊዜ ሕልም እንጂ ፥
እውነት አልመሰለንም ነበር ።
2 እጅግ በመደሰት የሐሤት መዝሙር
ዘመርን ፤
ስለዚህ ሌሎች መንግሥታት ፥
"እግዚአብሔር ታላቅ ነገር
አደረገላቸው" አሉን ።
3 በእርግጥም ብዙ ታላላቅ ነገሮችን
አድርጎልናል!
እጅግም ተደስተናል ።

4 እግዚአብሔር ሆይ!
ዝናም ለደረቅ ወንዝ ውሃን
እንደሚሰጥ
ምርኮአችንን መልሰልን ።
5 እያለቀሱ ዘር ለመዝራት የሄዱትን ፥
መከሩን ሲሰበስቡ እንዲደሰቱ
አድርግ ።

6 ዘሩን ተሸክመው ሲሄዱ ያለቅሱ
የነበሩት ፥
በደስታ እየዘመሩ ነዶአቸውን
ተሸክመው ይመለሳሉ ።

## ምዕራፍ 127

ስለ እግዚአብሔር ቸርነት የቀረበ ምስጋና

1 እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ፥
የቤት ሠራዎች ድካም ከንቱ ነው ፤
እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ፥
የከተማ ጠባቂዎች ትጋት ከንቱ ነው ።
2 በማለዳ እየተነሡና በምሽትም እየዘገዩ
ለኑሮ መድከም ከንቱ ነው ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር
ለሚወድዳቸው ሰዎች ፥
ገና ተኝተው ሳሉ ፥
የሚያስፈልጋቸውን ነገር
ያዘጋጅላቸዋል ።

3 ልጆች ከእግዚአብሔር የሚገኙ
ስጦታዎች ናቸው ፤
እውነተኛም በረከት ናቸው ።
4 ሰው በወጣትነቱ የሚወልዳቸው ወንዶች
ልጆች ፥
በወታደር እጅ እንዳሉ ፍላጻዎች
ናቸው ።
5 እንደነዚህ ፍላጻዎች የሆኑ ብዙ ልጆች
ያሉት ሰው የታደለ ነው ፤
ከጠላቶቹ ጋር በፍርድ አደባባይ
በሚከራከርበት ጊዜ ከቶ አይሸነፍም ።

## ምዕራፍ 128

ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚገኝ በረከት

1 እግዚአብሔርን የሚያከብሩና ትእዛዙን
በመጠበቅ የሚኖሩ ደስ ይበላቸው ።

2 ሠርተህ የምታፈራውን ትመገባለህ ፤
ደስታና ተድላም ታገኛለህ ።
3 ሚስትህ በቤትህ
እንደ ፍሬያማ የወይን ተክል
ትሆናለች ፤
ልጆችህም በማእድህ ዙሪያ
እንደ ወይራ ለምለም ቅርንጫፎች
ይሆናሉ ።
4 እግዚአብሔርን የሚያከብር
እንደዚህ የተባረከ ይሆናል ።

5 እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ!
የኢየሩሳሌምን ብልጽግና በሕይወትህ
ዘመን ሁሉ
እንድታይ ያድርግህ!
6 የልጆችህን ልጆች ለማየት
እንድትበቃ ያድርግህ ።

ሰላም ከእስራኤል ጋር ይሁን!

## ምዕራፍ 129

ከእስራኤል ጠላቶች ለመዳን የቀረበ ጸሎት

1 እስራኤል ሆይ! ከወጣትነትህ ጀምሮ
ጠላቶችህ እንዴት እንዳሳደዱህ
እስቲ ንገረን ።

2 "ከወጣትነቴ ጀምሮ ጠላቶቼ
በጭካኔ አሳደዱኝ ፤
ነገር ግን አላሸነፉኝም ።
3 ጀርባዬን በጅራፍ ተልትለው ፥
የታረሰ ማሳ አስመስለውታል ።
4 ነገር ግን እውነተኛ የሆነ እግዚአብሔር ፥
ከሀመፀኞች እስራት ፈትቶ ነፃ
አወጣኝ ።"

5 ጽዮንን የሚጠላ ሁሉ ይሸነፍ፤
ወደ ኋላውም ይመለስ።
6 በቤት ጣራ ላይ እንደሚበቅልና
ከማደጉ በፊት እንደሚደርቅ
ሣር ይሁን።
7 እንዲህ ሀይነቱን ሣር ማንም
አይሰበስበውም፤
ወይም ነዶውን እስሮ አይወስደውም።
8 በአጠገባቸው የሚያልፉት ሁሉ ለጽዮን
ጠላቶች
“እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤
እኛም በእግዚአብሔር ስም
እንባርካችኋለን”
አይሏቸውም።

## ምዕራፍ 130

የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለማግኘት
የቀረበ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ! ከጥልቅ ሐዘን
የተነሣ
ወደ አንተ እጮኻለሁ።
2 እግዚአብሔር ሆይ! ልመናዬን ስማ!
ዕርዳታህን ፈልጌ ስጮኽም
አድምጠኝ።
3 ኃጢአታችንን ብትከታተል፥
ማን ከፍርድ ሊያመልጥ ይችላል?
4 ነገር ግን አንተን በማክበር እንድንታዘዝህ
ይቅር ትለናለህ።

5 የእግዚአብሔርን ዕርዳታ በናፍቆት
እጠባበቃለሁ፤
በቃሉም እታመናለሁ።
6 የንጋትን ብርሃን ከሚጠባበቁ ሰዎች
ይልቅ፥
እኔ እግዚአብሔርን በናፍቆት
እጠባበቃለሁ።

7 እስራኤል ሆይ! ፍቅሩ ዘላለማዊ ስለሆነና
ሰዎችንም ለማዳን ዘወትር ዝግጁ
ስለሆነ፥
በእግዚአብሔር ታመን።
8 እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን
ከኃጢአታቸው ሁሉ ያድናቸዋል።

## ምዕራፍ 131

በትሕትና በእግዚአብሔር ስለ መታመን

1 እግዚአብሔር ሆይ! ትዕቢትን
አስወግጃለሁ፤
ከትምክሕትም ርቄአለሁ፤
ስለ ታላላቅ ነገሮች ወይም ላስተውለው
ስለማልችለው ከባድ ነገር
አልጨነቅም።
2 ጸጥታንና ሰላምን አግኝቻለሁ፤
እናቱ የታቀፈችው ሕፃን ጸጥ ብሎ
እንደሚተኛ፥
የእኔም ልብ በውስጤ ጸጥ ብሎአል።
3 እስራኤል ሆይ! አሁንና ዘላለም፥
በእግዚአብሔር ታመን።

## ምዕራፍ 132

ስለ ቤተ መቅደስ የቀረበ ውዳሴ

1 እግዚአብሔር ሆይ! ዳዊትን
አስታውሰው፤
የተቀበለውን መከራ ሁሉ አትርሳ።
2 እግዚአብሔር ሆይ! ለአንተ የገባውን
ቃል ኪዳንና
ሁሉን የምትችል የያዕቆብ አምላክ
ለሆንኸው
ለአንተ እንዲህ ሲል የተሳለውን
ስእለት አስታውስ፤
3-5 “ለእግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራ
እስከማዘጋጅ፥
ለያዕቆብ አምላክ ቤት እስከምሠራ
ድረስ፥
ወደ ቤት አልገባም፤
ወይም በአልጋ ላይ አልተኛም፤
ዕረፍት ወይም እንቅልፍ
አይኖረኝም።”

6 በቤተልሔም ሆነን ስለ ቃል ኪዳኑ
ታቦት ሰማን፤
በጃዕሪም ምድር አገኘነው።
7 ከዚህ በኋላ “ኑ ወደ እግዚአብሔር ቤት
እንሂድ!
በዙፋኑም ፊት እንስገድ!” አልን።

8 እግዚአብሔር ሆይ!
የኀይልህ ምልክት ከሆነችው
ከቃል ኪዳን ታቦት ጋር
ወደምታርፍበት
ወደ ቤተ መቅደስ ግባ።
9 ካህናትህ ዘወትር ቅኑን ነገር ያድርጉ፤
ሕዝብህም በደስታ “እልል!” ይበሉ።

10 ከአገልጋይህ ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን
ገባህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር ሆይ!
የመረጥኸውን ንጉሥ አትተወው።
11 ከዳዊት ጋር ከቶ የማይሻር ቃል ኪዳን
እንዲህ ስትል ገባህ፥

130፥8 ፦ ማቴ. 1፥21፤ ቲቶ 2፥14። 132፥6-10 ፦ 2ዜ.መ. 6፥41-42። 132፥11 ፦ 2ሳሙ. 7፥12-16፤
1ዜ.መ. 17፥11-14፤ መዝ. 89፥3-4፤ ሐ.ሥ. 2፥30።

ትውልድ ሁሉ ያስታውሱሃል ።
14 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳል ፤
ለአገልጋዮቹም ይራራል ።

15 የአረማውያን አማልክት ፥
ከብርና ከወርቅ በሰው እጅ የተሠሩ
ጣዖታት ናቸው ።
16 አፍ አላቸው ፥ አይናገሩም ፤
ዐይን አላቸው ፥ አያዩም ።
17 ጆሮ አላቸው ፥ አይሰሙም ፤
በአፍንጫቸውም መተንፈስ
አይችሉም ፤
18 የሠሩአቸውና የሚታመኑባቸው ሁሉ ፥
እንደነዚህ ጣዖቶች ይሁኑ ።

19 የእስራኤል ሕዝብ ሆይ !
እግዚአብሔርን አመስግኑ ፤
እናንተም የእግዚአብሔር ካህናት ፥
እግዚአብሔርን አመስግኑ ።
20 እናንተ ሌዋውያን ፥ እግዚአብሔርን
አመስግኑ ፤
እግዚአብሔርን የምታከብሩ ሁሉ ፥
እግዚአብሔርን አመስግኑ ።
21 እግዚአብሔርን በጽዮን አመስግኑት ፤
በመኖሪያው በኢየሩሳሌም
አመስግኑት ።

እግዚአብሔርን አመስግኑ !

## ምዕራፍ 136
### የምስጋና መዝሙር

1 ቸር ስለሆነ ለእግዚአብሔር ምስጋና
አቅርቡ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
2 ከአማልክት ሁሉ ለሚበልጠው አምላክ
ምስጋና አቅርቡ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
3 የጌቶች ጌታ ለሆነው አምላክ ምስጋና
አቅርቡ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።

4 እርሱ ብቻ ታላላቅ ተአምራትን
ያደርጋል ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
5 በጥበቡ ሰማያትን ፈጠረ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
6 ምድርን በጥልቅ ውሃዎች ላይ መሠረተ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
7 ፀሐይንና ጨረቃን ፈጠረ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
8 ፀሐይ በቀን እንዲያበራ አደረገ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
9 ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት እንዲያበሩ
አደረገ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።

10 የግብጻውያንን የበኲር ወንዶች ልጆች
ገደለ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
11 የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ አገር መርቶ
አወጣ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
12 በጠንካራ እጁ ፥ በብርቱ ክንዱም ይህን
አደረገ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
13 ቀይ ባሕርን ከፈለ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
14 ሕዝቡንም በመካከሉ አሳለፈ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
15 የግብጽን ንጉሥ ፈርዖንንና ሠራዊቱን
በቀይ ባሕር አሰጠመ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።

16 ሕዝቡን በበረሓ መራ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
17 ኀያላን ነገሥታትን ገደለ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
18 ታላላቅ ነገሥታትንም ደመሰሰ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
19 የአሞራውያንን ንጉሥ ሲሖንን ገደለ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
20 የባሳንንም ንጉሥ ዖግን ገደለ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
21 ምድራቸውን ሁሉ ለሕዝቡ ርስት
አድርጎ ሰጠ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
22 ለአገልጋዩ ለእስራኤል አወረሰ ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።

23 በተሸነፍን ጊዜ አልረሳንም ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
24 ከጠላቶቻችን እጅ ነፃ አወጣን ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።
25 ለሕያው ፍጥረት ሁሉ ምግብን ይሰጣል ፤
ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው ።

136፡1 ፦ 1ዜ.መ. 16፡34 ፤ 2ዜ.መ. 5፡13 ፤ 7፡3 ፤ ዕዝ. 3፡11 ፤ መዝ. 100፡5 ፤ 106፡1 ፤ 107፡1 ፤ 118፡1 ፤ ኤር. 33፡11 ።
136፡5 ፦ ዘፍ. 1፡1 ። 136፡6 ፦ ዘፍ. 1፡2 ። 136፡7-9 ፦ ዘፍ. 1፡16 ። 136፡10 ፦ ዘጸ. 12፡29 ።
136፡11 ፦ ዘጸ. 12፡51 ። 136፡13-15 ፦ ዘጸ. 14፡21-29 ። 136፡19 ፦ ዘኍ. 21፡21-30 ።
136፡20 ፦ ዘኍ. 21፡31-35 ።

